# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ማክሰኞ 83ኛ ዓመት ቁጥር 127 ጥር 7 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!













# የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ ከትናንት እስከ ዛሬ

**ሄለን ወንድምነው**
**ዜና ሐተታ**

ከሶስት ሺህ ዘመን በላይ ታሪክ አለው። ታሪኩም በአግባቡ ተሰንዶ በትውልድ ቅብብሎሽ ዛሬ ላይ ደርሷል። ነገንም በተተኪ ትውልድ ይሻገራል። ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም መከበርና ገጽታ ግንባታ ጉልህ ሚና አበርክቷል። አስተዋጽኦው በብዙዎች የድካም ውጤት የተገኘ ነው። በርካቶች በተሰጣቸው ጸጋ እውቀታቸውን፣ ጊዜያቸውንና ጉልበታቸውን ለግሰዋል።

የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ ከጥንታዊ ሥልጣኔ ጀምሮ ዛሬም ድረስ እየተሠሩ ባሉ የዲፕሎማሲ ሥራዎች፤ የኢትዮጵያ ስም በሌሎች ሀገራት በደማቁ እንዲጻፍ፣ ተሰሚነቷ እንዲጨምርና በባለብዙ ወገን ዲፕሎማሲ እንድትሳተፍ እድል ፈጥሯል።

የኢትዮጵያን ዲፕሎማሲ የከፍታ ጉዞ ለትውልድ ለማሳወቅ፣ የነገን የዲፕሎማሲ ሥራ የበለጠ ለማጠናከር በአይነቱ ልዩ የሆነ የዲፕሎማሲ ሳምንት አውደ ርዕይ ሰሞኑን በሳይንስ ሙዚየም ተከፍቷል። አውደ ርዕዩን ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ ጥር 2 ቀን 2016 ዓ.ም

የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

# ኢትዮጵያ ከመሳው አፍሪካ ጋር ያሳት የንግድ ልውውጥ በቅርቡ ወደ ከፍተኛ ደረጃ ይሸጋገራል

**ተስፋ ፈሩ**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- ኢትዮጵያ ከጎረቤት ሀገራትም ሆነ ከመላው አፍሪካ ጋር ያላት የንግድ ልውውጥ በቅርብ ዓመታት ውስጥ ወደ ከፍተኛ ደረጃ እንደሚያድግ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

ኢትዮጵያ ከመሳው ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

# “ከሶማሊላንድ ጋር የተደረገው የባሕር በር ስምምነት ጥቅሙ ፈርጀ ብዙ ነው”

- አቶ ሌንጮ ለታ

**ዋቅሹም ፍቃዱ**



<u>አዲስ አበባ</u>፡- ኢትዮጵያ ከሶማሊላንድ ጋር ያደረገችው የባሕር ብር ስምምነት ታሪካዊ የዲፕሎማሲ ስኬት ከመሆኑም በላይ ፈርጀ ብዙ ጥቅም መኖሩን ፖለቲከኛው አቶ ሌንጮ ገለጹ፡፡

አቶ ሌንጮ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፣ ኢትዮጵያ ከየትኛው ሀገር ጋር ስምምነት በመፍጠር የባሕር በር የማግኘት መብት አላት፡፡ ሶማሊላንድም በሕዝበ ውሳኔ የተመሠረተው የራሷ መንግሥት ያላት ሀገር በመሆኗ በሀገሯ ኢኮኖሚና ፖለቲካ ጉዳዮች ላይ የመወሰን ሙሉ መብት አላት፡፡ ኢትዮጵያ ከሶማሊላንድ ጋር ስምምነት መፍጠሯ ታሪካዊ

“ከሶማሊሳንድ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

# ኢትዮጵያና እንግሊዝ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነታቸውን ወደ ስትራቴጂካዊ አጋርነት ሊያሳድጉ ነው

**ሳሙኤል ወንደሰን**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- ኢትዮጵያና ዩናይትድ ኪንግደም ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነታቸውን ወደ ስትራቴጂካዊ አጋርነት ለማሳደግ የሚያስችላቸውን የመግባቢያ ስምምነት ለመፈራረም በዝግጅት ላይ መሆናቸውን አምባሳደር ተፈሪ መለሰ ገለጹ።

በዩናይትድ ኪንግደም የኢትዮጵያ አምባሳደር ተፈሪ መለሰ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ በሁለቱ ወገኖች መካከል ያለውን ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ወደ ላቀ ደረጃ ለማሳደግ የተለያዩ ሥራዎች እየተሠሩ ነው።

በሁለቱ ወገኖች መካከል ያለው የሁለትዮሽ ግንኙነት በጥሩ ሁኔታ የሚገኝ ሲሆን ያለውን ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ወደ ስትራቴጂካዊ አጋርነት ለማሳደግ የመግባቢያ ስምምነት ለመፈራረም የሚያስችል ዝግጅት በመጠናቀቅ ላይ ነው ብለዋል።

ኢትዮጵያና እንግሊዝ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል



አምባሳደር ተፈሪ መለሰ







ዜና

# በክልሉ የመስኖ መሠረተ ልማቶችን ሥራ ለማስጀመር እየተሠራ ነው

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**



አፋር፡- በአፋር ክልል ተገንብተው ሥራ ያልጀመሩ መሠረተ ልማቶችን ወደሥራ ለማስገባት እየተሠራ መሆኑን የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ዴኤታ ሰላማዊት ካሳ ገለጹ።

የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ዴኤታ ወይዘሮ ሰላማዊት ካሳ እንደገለጹት፤ በክልሉ ከዚህ በፊት ከፍተኛ ወጪ ወጥቶባቸው ተገንብተው በሚጠበቅባቸው ደረጃ አገልግሎት ሳይሰጡ የቀሩ የመስኖ አገልግሎት መስጫ መሠረተ ልማቶች ነበሩ። በአሁኑ ወቅት እነዚህን ፕሮጀክቶች ወደ ሥራ ለማስገባት የሚያስችሉ በርካታ ሥራዎች እየተከናወኑ ሲሆን ጥገናዎቹ በሚቀጥሉት ጥቂት ወራት የሚጠናቀቁ ይሆናል ሲሉም ገልጸዋል።

ወይዘሮ ሰላማዊት እንደገለጹት፤ እንደ ሀገር አስር ሚሊዮን ሄክታር በመስኖ ለማልማት የሚያስችል አቅም አለ። በተያዘው በጀት ዓመት ብቻ በበጋ መስኖ ሶስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ለማልማት እቅድ ተይዞ እየተሠራ ሲሆን በአሁኑ ወቅት ሁለት ሚሊዮን ሄክታር የሚደርስ መሬት ተዘጋጅቶ ዘር መዘራት ተጀምሯል ብለዋል። ይህንን ከግምት በማስገባትም መንግሥት ለዘርፉ በርካታ ድጋፎችን ሲያከናውን ቆይቷል።

የመንግሥት ዋነኛ ግብ በራስ አቅም አምርቶ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ ነው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታዋ፣ ይህንን ደግሞ በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ አምርቶ ማሳካት አይቻልም። በመሆኑም የተቀናጀ የመስኖ ሥራ ትልቅ ድርሻ ይኖረዋል። በዚህ ረገድ ትልቅ አቅም ካላቸው አካባቢዎች የአፋር ክልል አንዱ ነው ብለዋል።

በክልሉ ሰፊ የሚታረስ መሬት ተስማሚ የአየር ንብረትና ይህንን ሊያለማ የሚያስችል እምቅ የውሃ ኃይል እንዳለም ተናግረዋል።

አካባቢው በተደጋጋሚ በጎርፍ የሚጠቃ በመሆኑም ጎርፍ መከላከል የሚያስችሉ የመሠረተ ልማት ሥራዎችም እየተከናወኑ ይገኛል። እነዚህ እንቅስቃሴዎች ፕሮጀክቶቹ የሚጠበቅባቸውን ምርት በማስገኘት የአካባቢውን ነዋሪ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ይሆናል።

በተጨማሪም በአፋር ክልል በሌማት ትሩፋት ሥራዎች መርሃ ግብር በተለያዩ አካባቢዎች የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛል።

በዚህም በፌዴራል ደረጃ ባሉ ተቋማት ትብብር የሚተገበሩ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን የማህበረሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ የሚያደርጉ የእንስሳትና የዶሮ ርባታ ፕሮጀክቶች እየተከናወኑ ይገኛል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታዋ ፣ በዚህ ረገድ እየተከናወኑ ያሉ ሥራዎች አበረታች ለውጥ እያስመዘገቡ ይገኛል። በቀጣይም እነዚህ ጅምሮች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ተገቢው ትኩረት ተሰጥቶ ክትትልና ድጋፍ የሚደረግ ይሆናል ብለዋል።

በዚህ ረገድም መገናኛ ብዙኃን ከማህበረሰቡ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ለሚመለከታቸው አካላት በማድረስ የክትትል ሥራዎችን መሥራት እንደሚጠበቅባቸውም ተናግረዋል።

# ወልድያ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎቹን እየተቀበለ ነው

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- ወልድያ ዩኒቨርሲቲ በመደበኛ መርሐ-ግብር የሚማሩ ስድስት ሺህ ተማሪዎቹን እየተቀበለ መሆኑን አስታወቀ። የተማሪዎች ቅበላ ጥር ስድስት ቀን 2016 ዓ.ም መጀመሩ ተመላክቷል።

የወልዲያ ዩኒቨርሲቲ የሕዝብና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ሥራ አስፈጻሚ ብርሃን ደጀን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በክልሉ የተፈጠረውን አንጻራዊ ሰላም በመጠቀም ዩኒቨርሲቲው ከጥር ስድስት ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ ተማሪዎችን መቀበል ጀምሯል።

በክልሉ በነበረው የጸጥታ ሁኔታ ምክንያት በመደበኛው የትምህርት የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ተማሪዎችን ተቀብሎ የመማር ማስተማር ሂደቱን እንዳልቻለ አስታውሰው፤ አሁን ላይ በአማራ ክልል ያለውን አንጻራዊ ሰላም በመጠቀም ዩኒቨርሲቲው ስድስት ሺህ ተማሪዎችን ተቀብሎ ለማስተማር ዝግጅት እያደረገ ነው ብለዋል።

ነባር የሁለተኛና የሶስተኛ ዓመት ተማሪዎች እንዲሁም በ2015 ዓ.ም የአቅም ማሻሻያ ፕሮግራም ትምህርት ተከታትለው የማለፊያ ውጤት ያስመዘገቡ ተማሪዎች ወደዩኒቨርሲቲው መግባት መጀመራቸውን ተናግረዋል።

በ2014 ዓ.ም እና በ2015 ዓ.ም በተለያዩ ምክንያቶች ትምህርት አቋርጠው የነበሩ ተማሪዎች እና በ2015 ዓ.ም የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ወስደው የማለፊያ ውጤት አስመዝግበው በወልድያ ዩኒቨርሲቲ ለተመደቡ ተማሪዎች እየገቡ መሆኑን ጨምረው ገልጸዋል።

የተማሪዎች ህብረትና የተማሪ በጎ አድራጎት ማህበር አስፈላጊውን ባጅ አዘጋጅተው ተማሪዎችን መናኸሪያ እና በዩኒቨርሲተው መግቢያ በሮች ቅበላ እያደረጉላቸው መሆኑን ገልጸዋል።

በተጨማሪም የዩኒቨርሲቲውና የከተማው የጸጥታ አካላት ጋር ውይይት መደረጉን ጠቁመው፤ ለረጅም ጊዜ ተዘግተው የቆዩ የተማሪዎች ማደሪያ ክፍሎች ላይ አስፈላጊው የኬሚካል ርጭት፣ የቀለም ቅብና የማጽዳት ሥራ ተሠርቷል ብለዋል።

ተማሪዎች እንደገቡ የመማር ማስተማር ሂደቱን በቀጥታ ለማስጀመር የመማሪያ ክፍሎችን፣ መምህራንን እና አስፈላጊ የቤተ ሙከራ ግብዓቶች ዝግጁ መደረጋቸውን አስታውቀዋል።

ከመማር ማስተማር ግብዓቶች በተጨማሪም የምግብ ግብዓት ተማሪዎች ከመግባታቸው ቀድሞ ዝግጁ መደረጋቸውን አስረድተዋል።

ከጥር ስድስት ቀን እስከ ጥር ሰባት ቀን 2016 ዓ.ም መደበኛ ምዝገባ እየተከናወነ መሆኑን አንስተው፤ ጥር ስምንት ደግሞ በቅጣት ምዝገባ ይከናወናል ሲሉ የጊዜ ሰሌዳውን አስታውሰዋል።

አቶ ብርሃን እንደገለጹት፤ ጥር ዘጠኝ አጠቃላይ ገለጻ በመስጠት ከጥር 10 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ መደበኛ የመማር ማስተማር ሂደቱን ለማስቀጠል እቅድ ተይዟል።

ተማሪዎች ለአምስት ወር ያህል ከትምህርት ገበታ ርቀው የቆዩ መሆናቸውን አስታውሰው፤ ተማሪዎች አስፈላጊውን ዕውቀት አግኝተው የላቀ ውጤት እንዲያዝመዘግቡና ለመውጫ ፈተና እንዲዘጋጁ ጥረት ይደረጋል ብለዋል።



400 ረዳት ተማሪ ትራፊክ አስተናባሪዎች ተመርቀዋል

# በትራፊክ አደጋ ሕይወታቸውን ከሚያጡ ዜጎች 86 በመቶ እግረኞች ናቸው

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- በትራፊክ አደጋ ሕይወታቸውን ከሚያጡ ዜጎች መካከል 86 በመቶ እግረኞች መሆናቸውን የአዲስ አበባ ትራፊክ ማኔጅመንት ባለሥልጣን አስታወቀ።

የአዲስ አበባ ትራፊክ ማኔጅመንት ባለሥልጣን ሰሞኑን 400 ረዳት ተማሪ ትራፊክ አስተናባሪዎችን ለአንድ ወር አሠልጥኖ አስመርቋል።

የአዲስ አበባ ትራፊክ ማኔጅመንት ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር አቶ ከበበው ሚዴቅሳ እንደገለጹት፤ በኢትዮጵያ በትራፊክ አደጋ በዓመት ከአራት ሺህ በላይ ዜጎች ሕይወታቸውን ያጣሉ። በአዲስ አበባ ደግሞ በቀን አንድ ሰው ሕይወቱን ያጣል።

ዳይሬክተሩ በ2015 ዓ.ም የትራፊክ አደጋ ካለፈው ዓመት ጋር ሲነጻጸር የሞት አደጋን መቀነሱን ገልጸው፤ በ2015 ዓ.ም 408 ሰዎች በትራፊክ አደጋ ሕይወታቸው አጥተዋል። ይህ ከ2014 ዓ.ም ጋር ሲነጻጸርም ስምንት በመቶ በትራፊክ የሚደርስ የሞት አደጋ ቀንሷል ብለዋል።

የትራፊክ ግጭት ዋና ዋና መንስኤዎች መካከል በፍጥነት ማሽከርከር፣ የደህንነት ቀበቶ እና የልጆች የደህንነት መቀመጫ አጠቃቀም እንዲሁም ሞተር አሽከርካሪዎች የጭንቅላት መከላከያ ቆብ አለማድረግ እንደሚገኙበት ጠቅሰዋል።

የሞት አደጋ ከደረሰባቸው የመንገድ ተጠቃሚዎች ውስጥ እግረኞች 86 በመቶ እንደሚይዙ ገልጸው፤ እግረኞችን ከአደጋው ለመታደግ የተጠናከሩ ሥራዎች ይሠራሉ ብለዋል።

በዚህም ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ የትራፊክ አደጋ ለመከላከል ከትምህርት ቤቶች ጋር በጋራ እየሠራ እንደሚገኝና በተለያዩ ጊዜያቶች ተማሪዎችን በትራፊክ አገልግሎት ላይ እያሠለጠነ እንደሚገኝ ጠቅሰዋል።

ከ111ዱም ክፍለ ከተማ ለትራፊክ አደጋ ተጋላጭ ከሆኑ ትምህርት ቤቶች የተውጣጡ 400 ተማሪዎች የተግባር ሥልጠና በአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን በኩልና የንድፈ ሃሳብ ሥልጠና ደግሞ በትራፊክ ማኔጅመንት ባለሙያዎች በኩል አሠልጥኖ በትናንትናው እለት ማስመረቁን ገልጸዋል።

ተማሪዎቹ በትምህርት መግቢያና መውጫ ሰአት በትምህርት ቤቶች አካባቢ የትራፊክ አደጋ እንዳይከሰት ይሠራሉ ያሉ ሲሆን ባለሥልጣን መሥሪያቤቱም ድጋፍና ክትትል እንደሚያደርግላቸው ገልጸዋል።

ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ ባለፉት ዓመታት ለትራፊክ አደጋ ተጋላጭ ከሆኑ 200 ትምህርት ቤቶች የተውጣጡ ከአምስት ሺህ በላይ ረዳት ተማሪ የትራፊክ አስተናባሪዎችን አሠልጥኖ ወደ ሥራ አሰማርቶ ይገኛል።

ዳይሬክተሩ ተማሪዎቹ የመንገድ ትራፊክ ፍሰትን በማስተናበር መደበኛ የትራፊክ ፖሊሶችን በማገዝ እግረኛውን በተለይም ተማሪዎችን መደበኛ የእግረኛ መንገድ እንዲጠቀሙ የሚያግዙ ሲሆን ከዚህ ቀደም በተሠራ ሥራም በትምህርት ቤት አካባቢ የሚደርስ አደጋን መቀነስ መቻሉን ገልጸዋል።



ፎቶ: ገባቦ ገብሬ

ወይዘሮ ሊዲያ ግርማ

## በአዲስ አበባና በሸገር ከተሞች የጥምቀት በዓልን ያለጸጥታ ችግር ለማክበር ትኩረት ተደርጓል

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባና በሸገር ከተማ አስተዳደሮች የጥምቀት በዓል ያለምንም የጸጥታ ችግር ለማክበር ትኩረት መደረጉን ከሁለቱም ከተሞች የተውጣጡ የጸጥታ መዋቅርና አመራሮች ገለጹ።

በአዲስ አበባና በሸገር ከተማ አስተዳደሮች የጥምቀት በዓል ያለምንም የጸጥታ ችግር እንዲከበር ከሁለቱም ከተሞች የተውጣጡ የጸጥታ መዋቅርና አመራሮች የተሳተፉበት የምክክር መድረክ ትናንትና ተካሂዷል።

በምክክር መድረኩ ንግግር ያደረጉት የአዲስ አበባ ከተማ ሰላምና ጸጥታ አስተዳደር ቢሮ ኃላፊ ወይዘሮ ሊዲያ ግርማ ሁለቱ ከተሞች በተለያዩ የሥራ ዘርፎች በቅንጅት እየሠሩ መሆኑን ተናግረዋል።

ከጸጥታ ጋር ተያይዞ በተሠሩ የጋራ ሥራዎች ባለፉት ጊዜያት በርካታ በዓላትንና የተለያዩ ሁነቶችን ያለምንም የጸጥታ ችግር ማክበር እንደተቻለ አስታውሰው፤ በ2016 ዓ.ም የሚከበረውን የጥምቀት በዓልም ያለምንም የጸጥታ ችግር በሰላም ለማክበር ሁለቱ የከተማ አስተዳደሮች የጸጥታ መዋቅሮች ካለፈው ተሞክሮ ወስደው ይበልጥ እንደሚሠሩ ገልጸዋል።

የአዲስ አበባና ሸገር ከተሞች በሠሩት ቅንጅታዊ የጸጥታ ሥራ ባለፉት ጊዜያት ሃይማኖታዊና ባህላዊ የአደባባይ በዓላት ሠላማዊ በሆነ መንገድ መከበራቸውን ወይዘሮ ሊዲያ ተናግረዋል።

ምክክሩ የከተማ አስተዳደሮቹ የጋራ ሥራ በዩኔስኮ የተመዘበውን የአደባባይ በዓል የሆነው ጥምቀት ያለምንም የጸጥታ ችግር ሃይማኖታዊ ትውፊቱን ጠብቆ ለማክበር የሚደረገው ጥረት አካል መሆኑን አስረድተዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ ሰላምና ጸጥታ አስተዳደር ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ጌታሁን አበራ በበኩላቸው፤ በዓሉ ሃይማኖታዊ እሴቶች፣ ተቻችሎና ተከባብሮ በሠላም የመኖር ባህል ለዓለም ሕዝብ የሚታይበት ሥርዓት በመሆኑ ያለ አንዳች የጸጥታ ስጋት በሠላማዊ መንገድ መከናወን ይኖርበታል ብለዋል።

በበዓሉ ከሸገር ከተማ ወደ አዲስ አበባ፤ እንዲሁም ከአዲስ አበባ ወደ ሸገር ከተማ የሚሄዱ ታቦታት እንዳሉ የገለጹት አቶ ጌታሁን፤ ከሃይማኖት አባቶች፣ ከሀገር ሽማግሌዎች፣ ከወጣቶች፣ ከሃይማኖት መምህራንና ከህብረተሰቡ ጋር በዓሉን ሠላማዊ በሆነ መንገድ ለማክበር በትብብር ይሠራል ሲሉ ገልጸዋል።

አቶ ጌታሁን እንዳመለከቱት፤ በዓሉ በሠላም እንዲከበር ከአዲስ አበባ ከተማ፣ ከሸገር ከተማና ከፌዴራል ፖሊሲ፣ የሠላምና ጸጥታ አስተዳደር ጽህፈት ቤት፣ እንዲሁም ከሸገር ሚኒሻ፣ የቅጥር ጥበቃና ሌሎች ለጸጥታ ሥራ ከተደራጁና ከሰላም ወዳዱ ህብረተሰብ ጋር በቅንጅት እየተሠራ ይገኛል።

የህብረተሰቡን ደህንነት ለመጠበቅ፣ በአጎራባች አካባቢዎች ያለውን የትራፊክ ፍሰቶች ለመቆጣጠር፣ በዓሉ ያለ አንዳች የጸጥታ ችግር እንዲከበር እንዲሁም ወንጀል እንዳይከሰት ቅድመ ወንጀል መከላከል ላይ ያተኮረና ቅንጅታዊ አሠራርን መሠረት ያደረገ የማስፈጸሚያ እቅድ በጋራ መዘጋጀቱን ገልጸዋል።

ከሁለቱ ከተሞች የተውጣጡ የጸጥታ መዋቅር አካላት በዓሉ በሠላም እንዲጠናቀቅ በትኩረት እንደሚሠሩ በምክክር መድረኩ ላይ ተናግረዋል።

# በጎንደር የጥምቀት በዓልን በድምቀት ለማክበር ዝግጅት ተደርጓል

**ማህሌት ብዙነህ**



አዲስ አበባ፡- የ2016 ዓ.ም የጥምቀት በዓልን በደመቀ ሁኔታ በጎንደር ከተማ እንዲከበር የዝግጅት ሥራዎች እየተጠናቀቁ መሆናቸውን የጎንደር ከተማ አስተዳደር አስታወቀ።

የጎንደር ከተማ አስተዳደር የመንግሥት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች መምሪያ ኃላፊ አቶ አበበ ላቀው ለኢትዮጵያ ድርጅት እንደገለጹት፤ የጥምቀት በዓልን በደመቀ ሁኔታ ለማክበር በከተማ ደረጃ በከንቲባ የሚመራ አንድ ዐብይ ኮሚቴ እና ስምንት ንዑሳን ኮሚቴዎች ተደራጅተው ወደ ሥራ በመግባት የዝግጅት ሥራዎች እየተጠናቀቁ ናቸው።

በተለይም በጎንደር ፋሲለደስ ባህረ ጥምቀት በሚከናወንበት ሥፍራ የሚያስፈልጉ የግንባታ፣ የጽዳት እና ሌሎች ጊዜያዊ ሥራዎች ተጠናቅቀዋል ብለዋል።

አቶ አበበ፤ በዓሉን ለመታደም የሚመጡ እንግዶችን ለመቀበል ከአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ጋር አስፈላጊው ውይይት መደረጉን አስታውቀው፤ በዚህም እንግዶችን ተቀብሎ ለማስተናገድ ከባለፉት ዓመታት በተለየ መንገድ ዝግጁ መሆናቸውን ማረጋገጥ መቻሉን ገልጸዋል።

አገልግሎት ሰጪዎች ለበዓሉ ተሳታፊዎች የተሟላና ቀልጣፋ አገልግሎት በተመጣጣኝ ዋጋ ለመስጠት መዘጋጀታቸውን አስታውቀዋል።

ኃላፊው በተጨማሪም ከክልሉ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ጋር በጋራ በተሠራ ሥራም ክብረበዓሉን በከተማው ለመታደም ለሚመጡ ጎብኚዎች ከላሊበላ በቀጥታ ጎንደር የአየር ትራንስፖርት የተጀመረ መሆኑንም አስታውቀዋል።

እንዲሁም በከተማው የተሟላ የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት እየተሠራ ሲሆን ከአየር ማረፊያ ሆቴል የሚያደርስና ከተማ ውስጥ ለውስጥ የሚያስጎበኙ በቂ የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት ዝግጅት ተደርጓል ብለዋል።

አቶ አበበ እንደገለጹት፤ በዓሉ የከተማውን የቱሪዝም ኢንዱስትሪን ለማነቃቃት ትልቅ ፋይዳ አለው። ይህንንም ለመጠቀም ሰላም ዋና መሠረት ሲሆን ለዚህም ሕዝቡ የጸጥታው ባለቤት እንደሆነ በተደጋጋሚ በተዘጋጀ መድረክ ተረጋግጧል።

እንግዶች የጥምቀት በዓልን በከተማው ከማክበር ባለፈ ቆይታቸውን የሚያራዝምባቸው፣ የአካባቢውን ጸጋ የሚመለከቱበት ብሎም በዘርፉ ላይ ኢንቨስት የሚደርጉበትን ሁኔታዎች መመቻቸታቸውንም ነው የገለጹት።

ከበዓሉ በፊት የባህል ሳምንት መድረክ የሚዘጋጅ መሆኑን ጠቁመው፤ ሰፊ ማህበረሰብ የሚሳተፍበት በመሆኑ የዝግጅት ሥራዎች እንደተሠሩ አቶ አበበ አስታውቀዋል።

እንዲሁም በዓሉን ምክንያት በማድረግ በበዓሉ ማግስት በከተማ ደረጃ የኢንቨስትመንት ፎረም ይካሄዳል። በዚህ መድረክም እንግዶችን በኢንቨስትመንት ለማሳተፍ በግልጽ ጨረታ ከ 12 ነጥብ 7 ሄክታር በላይ መሬት በሊዝ ለባለሀብቶች ለማስተላለፍ ሰፊ ዝግጅት ተደርጓል ብለዋል።

በአሁኑ ጊዜ ጎንደርና አካባቢው በመደበኛና ሰላማዊ እንቅስቃሴ ላይ የሚገኝ ሲሆን በከተማው የተሟላ አገልግሎት እየተሰጠ ነው። በመሆኑም እንግዶች ያለምንም ስጋት በዓሉን ማክበርና በአካባቢው የሚገኙ የቱሪስት መዳረሻዎችን መጎብኘት የሚችሉ መሆኑን በመገንዘብ እንዲጎበኙ ጥሪያቸውን አቅርበዋል።

# የኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ ታሪክ የሚደነቅና ለሌሎች ሀገራት ተሞክሮ የሚሆን ነው

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ከጥንት እስከ ዛሬ ያከናወነችው የዲፕሎማሲ ሥራ የሚደነቅና ለሌሎች ሀገራት ተሞክሮ የሚሆን ነው ሲሉ የዲፕሎማሲ ሳምንት አውደ ርዕይን የጎበኙ የውጭ ሀገራት ዜጎች ገለጹ።

“ዲፕሎማሲያችን ለብሔራዊ ጥቅማችን” በሚል መሪ ሃሳብ በሳይንስ ሙዚየም የተዘጋጀው የዲፕሎማሲ ሳምንት አውደ ርዕይ በሀገር ውስጥና በውጭ ዜጎች ተገብኝቷል።

አውደ ርዕዩን የጎበኙት በኢትዮጵያ የሌሴቶ ኤምባሲ ዋና ፀሐፊ ሞኮሆ ሬቤካ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ አውደ ርዕዩ ኢትዮጵያ በዲፕሎማሲ ሥራ ያከናወነችውንና ከሌሎች ሀገራት ጋር ያላትን ግንኙነት በስፋት የሚያስረዳ ነው።

ኢትዮጵያ ከጥንት እስከ ዛሬ በዲፕሎማደሲ ሥራ ያከናወነችው ተግባር የሚደነቅ ነው ያሉት ፀሃፊዋ፤ በባለብዙ ወገን ዲፕሎማሲ የአፍሪካ ህብረትን መመሥረቷን ለአብነት አንስተዋል።

ኢትዮጵያ በጋራ መልማትንና በጋራ ማደግን መርህ አድርጋ በአፍሪካ ህብረት እና በሁለትዮሽ ግንኙነት እያከናወነች ያለው የዲፕሎማሲ ሥራ የሚደነቅ መሆኑን ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ በየዘመኑ በሠራቻቸው የዲፕሎማሲ ሥራዎች ብሔራዊ ጥቅሟን በማስከበርና ገጽታዋን ከመገንባቷም በተጨማሪ ለጥቁር ሕዝቦች ነጻ መውጣት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረከተች ሀገር መሆኗን የሚያስረዳ አውደ ርዕይ መሆኑን ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ ያላትን ባህልና ታሪክ በአግባቡ ሰንዳ ለትውልድ ማስተላለፍ እንዳለባት ጠቁመው፤ ሌሎች የአፍሪካ ሀገራትም ከኢትዮጵያ ዲፕሎማሲያዊ ጉዞ ሊማሩ ይገባል ብለዋል።



ሞኮሆ ሬቤካ



ሴንጊዝ ፖላት

በአዲስ አበባ የቱርክ የትብብርና ማስተባበሪያ ኤጀንሲ የአዲስ አበባ ጽህፈት ቤት የፕሮግራም አስተባባሪ ሴንጊዝ ፖላት በበኩላቸው እንደገለጹት፤ የዲፕሎማሲ ሳምንት አውደርዕዩ ኢትዮጵያ የረጅም ዘመን የዲፕሎማሲ ታሪክ ባለቤት መሆኗን የሚያስረዳ ነው።

ከንግሥተ ሳባ ጀምሮ እስካሁን ድረስ ያለው የዲፕሎማሲ ውጣ ውረድ በፎቶ፣ በቪዲዮና በጹሁፍ ተቀናጅቶ ከመቅረቡም ባለፈ አስጎብኚዎች በሚረዱበት ቋንቋ ገለጻ ስላደረጉላቸው የኢትዮጵያን ታሪክ በአግባቡ መረዳታቸውን ተናግረዋል።

አውደ ርዕዩ ኢትዮጵያ በዲፕሎማሲ ሥራ ትናንት ምን አከናወነች፣ ዛሬ ምን እሠራች ነው፣ ነገስ ምን ይጠበቃል የሚለውን የሚያስረዳ መሆኑን አስታውቀዋል።

ኢትዮጵያ በተለያዩ ዘመናት ያደረገችው የዲፕሎማሲ ሥራ ለሌሎች ሀገራት ተሞክሮ እንደሚሆን ገልጸው፤ ቱርክና ኢትዮጵያ በፖለቲካውና በንግዱ ዘርፍ ያላቸው የሁለትዮሽ ግንኙነትም ተጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባ አመላክተዋል።

የዲፕሎማሲ ሳምንት አውደ ርዕዩን የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ ጥር 2 ቀን 2016 ዓ.ም መርቀው የከፈቱት ሲሆን፤ እስከ ጥር 24 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ ለሕዝብ ክፍት ሆኖ ይቆያል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ተፎካካሪ ፓርቲዎች ስባህር በር ስምምነቱ የሰጡት ድጋፍ ምስጋናና ዕውቅና ሊሰጠው የሚገባ ነው!

ሀገር ጸንታ የምትኖረው ዜጎችዋ ለብሄራዊ ጥቅማቸው በሁለንተናዊ መልኩ በቁርጠኝነት መንቀሳቀስ ሲችሉ ነው ። ይህ ቁርጠንኝት በሰላም ወቅት የሀገርን ፖለቲካዊ ፣ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ማሳደግን ታሳቢ የሚያደርግ ፤ በችግር ወቅት ሕይወትን መስዋእት አድርጎ መስጠትን የሚጠይቅ ነው።

ብሄራዊ ጥቅም ከተወሰነ ቡድን ወይም በአንድ ወቅት በሥልጣን ላይ ካለ ፤ በሌላ ወቅት ከሚሰናበት መንግሥት ጋር የሚቆራኝ አይደለም። ከዚህ ይልቅ አሁን ያለውንና ወደፊት የሚመጣውን ትውልድ ዕጣ ፈንታ በመወሰን ሂደት ውስጥ ወሳኝ አቅም ነው። የትኛውም ማኅበረሰብ እንደ ማኅበረሰብ እስከ ድክመትና ጥንካሬው ፤ ልዩነቱና አንድነቱ ፤ በጋራ የሚቆምበት የጋራ አጀንዳው ነው።

ከመንግሥት ጋር ስለተኮራረፍን ፤ መንግሥት የሚያራምደው የፖለቲካ እሳቤ ስለማይስማማን ፤ ወይም አሁናዊ ሀገራዊ እውነታዎች ጥላ ያጠላበት ስለመሰለን ፤ እና ሌሎች መሰል ምክንያቶች አሳልፈን ለሌሎች የምንሰጠውም አይደለም ። ለአደጋዎች ሲጋለጥም አይተን እንዳላየን የምናልፈው አይደለም።

ብሄራዊ ጥቅም እንደ ቃሉ ብሔራዊ ጥቅም ነው ፤ የሕዝብ እና የሀገር ከዚያም ባለፈ የትውልዶች ጥቅም ነው። የራሳችን ፤ የወለድናቸው ልጆቻችን እና የልጅ ልጆቻቸው ጥቅም ነው። ይህ በትናንቱም ሆነ በአሁናዊው ዓለም የነበረና ያለ ፤ ዜጎች በየትኛውም መመዘኛ ለድርድር የማያስቀምጡት እውነታ ነው።

በተለይም ባለንበት ዘመን ዓለም አቀፋዊ እውነታው፤ በሁሉም አቅጣጫና እሳቤ ብሔራዊ ጥቅም የነገሮች ሁሉ መመዘኛ እየሆነ ባለበት ፤ ይህንን ጥቅም አሳልፎ መስጠት ፤ ብሩህ ስለሆኑ ነገዎች ተስፋ ማድረግ ቀርቶ ፤ ዛሬን እንደሀገር አሸንፎ ቆሞ መገኘት ትልቅ ፈተና እንደሚሆን ይታመናል።

የትኛውም ሀገር እንደሀገር ብሔራዊ ጥቅሞቹ አደጋ ውስጥ ሲወድቁ ፤ ዜጎች የትኛውንም አሁናዊ ችግሮቻቸውን የይደር አጀንዳ አድርገው ለብሔራዊ ጥቅማቸው በሁለንተናዊ መልኩ ዘብ የመቆም ኃላፊነት አለባቸው። ይህ ኃላፊነት ሀገርን በተስፋዋ ላይ የማቆምና የማጽናት ኃላፊነትም ጭምር ነው።

ይህ እውነት በኛ ሀገር የረጀም ሀገረ መንግሥት ትርክት ውስጥ ትልቅ ስፍራን የያዘ ነው። ትውልዶች በብዙ ልዩነቶች ፤ ከዚያም ባለፈ ፤ የከፋ በሚባሉ ውስጣዊ ችግሮች በገዘፉባቸው ቀናቶች ውስጥ ብሔራዊ ጥቅሞቻቸውን (እንደ ሀገር) የሚገዳደሩ ስጋቶችና አደጋዎች ሲያጋጥሟቸው ፤ የውስጥ ችግሮቻቸውን በይደር አስቀምጠው ለብሔራዊ ጥቅሞቻቸው ቅድሚያ በመስጠት አሁን ያለችውን ሀገር አስረክበውናል

በተጻራሪው ለብሔራዊ ጥቅሞቻችን ቅድሚያ በለመስጠታችን ፤ ጊዜ ፈጥሮ ለሚሽረው ፤ ዛሬ ለሚፈጠሩ ቅሬታዎችና መሻቶች ስንል ከሄድንባቸው ያልተገቡ መንገዶች የተነሳ የቀደሙት አባቶቻችን በውድ ዋጋ ያስረከቡንን የብሔራዊ ጥቅሞቻችን መሠረቶች አጥተን አሁን ላይ ያልተገባ ዋጋ እንድንከፍል እየሆንን ያለበት ሁኔታ የአደባባይ ሚስጥር ነው።

ይህ እውነታ ዛሬ ላይ ያለውን ትውልድ ብቻ ሳይሆን መጪዎቹን ትውልዶች ጭምር ሊፈታተን የሚችል ከፍ ያለ ተግዳሮት እንደሆነ ፤ በተለይም ተለዋዋጭ በሆነው የዓለም ፖለቲካ ውስጥ የሀገርን ሆነ የትውልዶችን ዕጣ ፈንታ የከፋ ስጋት ውስጥ ሊከት እንደሚችል ፤ ሀገርን እንደ ሀገር ጸንታ እንዳትቆም የማድረግ አቅሙም ከፍያለ እንደሆነ ይታመናል ።

ይህ በአይነቱ በብሄራዊ ጥቅም ላይ የሚከሰት ስጋት በተለይም በድህነትና በኋላቀርነት ውስጥ ብዙ ዋጋ ለመክፈል ለተገደዱ ፤ ይህንን ችግራቸውን ተሻግረው ነገዎቻቸውን የተሻሉ ለማድረግ ተስፋ ለሚያደርጉ ሕዝቦች ትልቅ ፈተና እንደሚሆን ፤ ከመጡበት የድህነትና የኋላቀርነት አዙሪት ለመውጣት የሚያደርጉትን ትግል ተስፋ ቢስ ሊያደርግ ይችላል።

ከዚህ አንጻር መንግሥት እንደመንግሥት ከትናንት ተንስቶ ፣ ዛሬን አይቶና ነገዎቻችን አሻግሮ ሀገርን ተጠቃሚ የሚያደርጉ ስትራቴከጂክ አቅሞችን በመገንባት ሂደት ላይ በስፋት እየሠራ ይገኛል። በዚህም ሀገር እንደ ሀገር አስተማማኝ እና ቀልጣፋ የወደብ አማራጭ አገልግሎት የምታገኝበትን መንገድ በማፈላለግ ላይ ነው፤ ይህንን ታሳቢ ባደረገ መንገድ በአካባቢው ለሚገኙ ወንድም ጎረቤት ሀገራት ጥሪ አቅርቧል።

ጥሪው ከሁሉም ባላይ የአካባቢው ሀገራት ያላቸውን አቅም ይዘው በጋራ ተጠቃሚነት መርህ ሕዝቦቻቸውን ተጠቃሚ ማድረግ የሚያስችላቸው ፤ ሀገራቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ ትልቅ የኢኮኖሚ አቅም ሆነው የሚወጡበትን ዕድል የሚፈጥር ነው ።

ይህን ከኢትዮጵያ ሕዝብ የማንነት እሴቶች የሚመነጨውን አብሮ የመልማት ጥሪ ፤ ተፎካካሪ ፓርቲዎች ተቀብለው ፤ ለተግባራዊነቱ ያሳዩት ቁርጠኝነት ፤ ከሁሉም በላይ ትውልዱ እንደቀደሙት አባቶች የቱንም ያህል ልነቶች ቢኖረው ፤ በብሔራዊ ጥቅሞቹ ላይ የማይደራደር መሆኑን በተጨባጭ ያሳየ ነውና ከፍያለ እውቅናና ክብር ሊሰጠው የሚገባ ነው!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የሕዝብ ግንኙነት ሠራተኞች ሙያዊ ኃላፊነታቸውን ሊወጡ ይገባል

ቲሻ ልዑል

የሕዝብ ግንኙነት ሥራ አንድ ተቋም ለትርፍ የተቋቋመ ይሁን አገልግሎት መስጠትን መነሻ ያድረገ ፣ ተቋሙ ከሕዝቡና ከተገልጋዩ ማሕበረሰብ ጋር ያለውን ግንኙነት ሚዛን ለመጠበቅና የጋራ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ የግድ አስፈላጊ ነው።

በሳን ጆሴ ዩኒቨርሲቲ የጋዜጠኝነትና ተግባቦት መምህር የሆኑት ፕሮፌሰር ማቲው ካቦት Mathew Cabot የሕዝብ ግንኙነት ሥራ የሁለት ወገን ተግባቦት (two-way communication) መርህ ላይ የተመሠረተና ለመልካም ገፅታ ግንባታ፣ የተቋሙን ስምና ክብር ለማጉላት፣ ለግንዛቤ ፈጠራ፣ ለማስተማር፣ የሕዝብ አመኔታን መፍጠር፣ አገልግሎትንና ጥሩ ሥራን ማስተዋወቅ፣ ተደራሹን የማነሳሳት ሥራ ለመሥራት መነሻ መርህ እንዳለው ይገልፃሉ።

ሕዝብ ግንኙነት የሁለት ወገን ተግባቦት መርህን መሠረት ያደረገ እንደመሆኑም ራስን ከመሸጥ ባለፈ ከሕዝቡ ወይም ከተገልጋዩ ሃሳብ በመውሰድና አስተያየት በመቀበል አገልግሎት ለማሻሻል አቅም ይፈጥራል።

በሀገራችን አንዳንድ ተቋሞች ከሌሎች በበለጠ መልኩ እየደከሙና እየሠሩ ሥራቸው ስለማይገለፅ በሕዝብ ወይም በተገልጋዩ ማሕበረሰብ በኩል ያላቸው ተቀባይነት ሲያድግ አይታይም። ወይም እየሠሩ ምንም መሥራት እንደማይችሉ ሲቆጠሩ ይታያል።

አንዳንድ ተቋማት ደግሞ የወርና የዓመት የሥራ ግምገማ ሪፖርት ከማስተላለፍ በዘለለ ያሉበትን ቁመና እየሰጡ ያሉትን አገልግሎት በሚያሳይ ደረጃ ሲሠሩ አይታይም። የሕዝብ ግንኙነት ሥራ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ብቁ በሆነ ባለሙያ መመራት አለበት። አንዳንድ ተቋማት በድካማቸው በሥራቸው ልክ እንዳይገለጹና መልካም ሥራቸውና ለሕዝብ እየሠጡት ያሉት አገልግሎት ከሥራ እንዳይቆጠር ያደረገው ደረጃውን የጠበቀ ሥራ በብቁ ባለሙያ አለመሥራታቸው ነው። ይህ ምስል የአብዛኞቹ የሀገራችን ተቃማት ነፀብራቅ ነው።

በአሁኑ ወቅት መረጃ በሰው ልጅ የእለት ተለት ኑሮ ውስጥ ያለው አስተዋፅኦ ከፍተኛ መሆኑ አጠያያቂ አይደለም። ከእለቱ የአየር ሁኔታ እስከ ሀገራዊ ጉዳዮች ድረስ ማህበረሰቡ ባለበት አካባቢና ሀገር ምን እየተካሄደ እንደሆነ ማወቅ የሚችለው ሚዲያዎች በሚሰጡት መረጃ ነው። የሚዲያ ተቋማት ወደ ማህበረሰቡ የሚያደርሱትን መረጃ ከሚያገኙባቸው የተለያዩ ምንጮች መካከል የሕዝብ ግንኙነት በግንባር ቀደምትነት ይጠቀሳል።

ሚዲያዎች አንድ ተቋም ምን እየሠራ እንደሆነ ፤ ሥራዎቹም በምን ደረጃ ላይ እንዳሉ መረጃ ከሚያገኙባቸው መንገዶች መካከል የተቋማቱ የሕዝብ ግንኙነት ባለሙያዎች ተጠቃሽ ናቸው። የሕዝብ ግንኙነት ባለሙያዎችም መረጃዎችን በፍጥነትና በጥራት ለመገናኛ ብዙኃን የመስጠት ትልቅ ሙያዊ ኃላፊነትም ግዴታም አለባቸው ።

በእርግጥ ለብዙዎች የሕዝብ ግንኙነት ዋናው ዓላማ የተቋምን ገፅታ መገንባት ነው። የተቋሙን ስኬታማነት አስጠብቆ ለማስኬድ ሙያዊና ስትራቴጂያዊ ስልቶችን ቀይሶ በተገልጋዩ ዘንድ በጎ እይታ በተቋሙ ላይ እንዲኖረው ማስቻል ነው። ይህ በአብዛኛውን በቢዝነስ ተቋማት ጎልቶ የሚታይ ነው።

ይህ ሙያዊ አገልግሎት ከፍ ባለ መልኩ በሕዝብና በመንግሥት መካከል ያለውን ግንኙነት በማሳለጥ ሂደት የሚኖረው አስተዋጽኦ ከዚህ ከፍያለ እንደሚሆን ይታመናል። በተለይም በዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ሂደት ባለ ማህበረሰብ ውስት የሚኖረው ፋይዳ ከፍ ያለ ነው።

አንድ የሕዝብ ግንኙነት ባለሙያም በመንግሣት እና በሕዝብ መካከል እንደድልድይ ሆኖ በማገልገል መልካም ግንኙነት የመፍጠር ሥራ መሥራት ይጠበቅበታል። የመንግሥትን ፖሊሲና ስትራቴጂ እንዲሁም የእለት ተእለት እንቅስቃሴ ለሕዝብ ግልፅ በሆነ መንገድ የማሳወቅ ኃላፊነትም አለበት።

ለዚህ ዓላማውም የሕትመትና የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎችን ጨምሮ ዘመኑ ያፈራቸውን ዲጅታል የሚዲያ አመራጮች ይጠቀማል። በተለይም ከተቋሙ የበላይ አመራሮች ጋር የጠበቀ ግንኙነት በመፍጠር በእቅድ ተደግፎ አስፈላጊውን ወቅታዊ መረጃዎች፤ በጥራትና በፍጥነት ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርስ የማድረግ ከፍ ያለ ኃላፊነት አለበት።

ወደ ዋናው ሃሳቤ ስመለስ፤ የሕዝብ ግንኙነት ባለሙያዎች የሚዲያ ተቋማት በጠየቋቸው ጊዜ መረጃ የመስጠት ወይም መረጃውን ከሚሰጠው አካል ጋር የማገናኘት ኃላፊነት እንዳለባቸው በዚህ ጽሁፍ የማሳውቀው አዲስ እውነታ አይደለም፤ የነበረና ያለ ነው። ትልቅ ጥያቄ እየሆነ የመጣው ግን በአሁኑ ወቅት ይህንን ኃላፊነታቸው አውቀው በአግባቡ ለሚዲያ ተቋማት መረጃ የሚሠጡ የተቋማት የሕዝብ ግንኙነት ባለሙያዎች ምን ያህል ናቸው የሚለው ነው።

በአንድ ወቅት የኢትዮጵያ ሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም ዋና እንባ ጠባቂ የሆኑት ዶክተር እንዳለ ኃይሌ በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር ባደረጉት ቆይታ በ2015 በጀት ዓመት ብቻ የመረጃ ነፃነት የሚመለከቱ 141 አቤቱታዎች ለተቋሙ መቅረቡንና እነዚህ አቤቱታዎች የመገናኛ ብዙኃንን ጨምሮ ለተለያዩ የምርምር ሥራዎች መረጃ ጠይቀው በተከለከሉ ግለሰቦች የቀረቡ ጥያቄዎች መሆናቸውን ተናግረው ነበር።

የመረጃ ነፃነት መብት አዋጁ በሚፈቅደው ልክ ተግባራዊ እየተደረገ እንዳልሆነ እና ይህንን ባለማድረጋቸው ከበርካታ የመገናኛ ብዙኃን ቅሬታ ለተቋሙ እንደሚቀርብ ገልፀው፤ የመንግሥት አስፈፃሚ አካላት በእጃቸው ያለውን መረጃ የመገናኛ ብዙኃንን ጨምሮ ለሚጠይቋቸው ዜጎች መስጠት እንዳለባቸው አዋጁ፤ የመረጃ ነፃነት አዋጁ እንደሚያስገድድም አስረድተዋል።

“የመረጃ ነፃነት አዋጁ የመገናኛ ብዙኃን መረጃ በጠየቁ በ10 ቀናት ውስጥ፤ እንዲሁም ማንኛውም ዜጋ በ30 ቀን ውስጥ የጠየቁትን መረጃ የማግኘት መብት እንዳላቸው ያስቀምጣል። ሆኖም ለመገናኛ ብዙኃን የተቀመጠው የአስር ቀን ገደብ መረጃን በወቅቱ ወደ ማሕበረሰቡ እንዳያደርሱ የሚያደርግ ነው። ይህንን መሠረት አድርገን አዋጁ በራሱ ክፍተት እንዳለበት በመመርመር እንዲሻሻል ሃሳብ አቅርበናል” ብለው ነበር።

የመረጃው ባለቤት የተጠየቀውን መረጃ በአግባቡና በሚፈለገው ጊዜ መስጠት ካልቻለ ለሀሰተኛ መረጃ መበራከትና በማህበረሰቡ ዘንድ ለሚፈጠር ብዥታ ዋና ምክንያት ይሆናል። የሚዲያ ተቋማት የተቋቋሙበት አንዱ ዓላማ ለማህበረሰቡ ትክክለኛ እና የጠራ መረጃ ለመስጠት ነው። በመሆኑም ይህንን ለማድረግና ማህበረሰቡን ከሀሰተኛ መረጃ ለመከላከል ትክክለኛውን መረጃ ለማወቅና ለሕዝብ ለማድረስ መረጃን በጠየቁበት በወቅት በፍጥነት ማግኘት አለባቸው።

ይህ ደግሞ መገናኛ ብዙኃኑን በቀጥታ ከተቋማት የሕዝብ ግንኙነት ባለሙያዎች ጋር የሚገናኝ ነው። እነሱ የሚፈለገውን መረጃ አግባብ ባለው መንገድ በኃላፊነት መንገድ በፍጥነትና በጥራት መስጠት ካልቻሉ ነገሩ “ላም አለኝ በሰማይ” አይነት እንደሚሆን ለመገመት የሚከብድ አይደለም።

በችግሩ ዙሪያ ሁሉንም የሕዝብ ግንኙነት ባለሙያዎች በአንድ ላይ መውቀስ አይቻልም። ሥራቸውን አውቀው በኃላፊነት ስሜት የሚሠሩ በርካታ ባለሙያዎች አሉ። በተለይም ጊዜው ያበረከተውን የቴክኖሎጂ ውጤት በመጠቀም እንቅስቃሴ የሚያደርጉ፣ የዕለት ውሏቸውን፣ አስፈላጊ ውሳኔዎችን በተመለከተ መረጃውን በተገቢው መንገድና ፍጥነት የሚያስተላልፉ ተቋማትም አሉ።

ይሁንና ከዚህ በተቃራኒ አንዳንድ ባለሙያዎች መረጃን ለሚዲያ ተቋማት ለመስጠት ሲበዛ ዳተኛ ሆነው ይታያዩ። ይህን ተከትሎም በርካታ መረጃዎች ሕዝብ ጋር ሳይደርሱ ይቀራሉ። የመረጃ መዛነፎችም ያጋጥማሉ።

መረጃን በመደበቅና ለሚዲያዎች በሮች ዝግ እንዲሆኑ ማድረግ መንግሥት እየሠራ ያለውን ሥራ እና ያለበትን ደረጃ ሕዝብ እንዳያውቅ ስለሚያደርግ ሊታሰብበት ይገባል። በመንግሥትና በሕዝብ መካከል ያለውን ግንኙነት ጠንካራ ለማድረግና በየጊዜው የደረሰበትን ደረጃ በቀላሉ ለሁሉም የማህበረሰብ ክፍል ለማድረስ ያለው ተመራጭ መንገድ ለሚዲያዎች በር መክፈትና አስፈላጊውን መረጃ መስጠት ነው።

የሕዝብ ግንኙነት ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመተግበር በተለይ ጎበዝ የተባሉት የመጡበትን መንገድና የገጠማቸው እንቅፋቶች እንዲሁም የተሻገሩበትን ዘዴ በአግባቡ መቃኘትና የልምድ ልውውጥ ማድረግም ይኖርባቸዋል።

# ኢትዮጵያ ከመላው አፍሪካ ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር ገብረመስቀል ጫላ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ ከጎረቤት ሀገራትም ሆነ ከመላው አፍሪካ ጋር ያላት የንግድ ልውውጥ እያደገ የመጣና በቀጣይም እየሰፋ የሚሄድ በመሆኑ በቅርብ ዓመታት ውስጥ ወደ ከፍተኛ ደረጃ ያድጋል ተብሎ ይጠበቃል::

ለኢትዮጵያ ትልቁ የግብይትና የድርድር መድረክ የአፍሪካ ነጻ የንግድ ቀጣና ነው ያሉት ሚኒስትሩ፤ ስምምነቱ ከተፈረመ ቆይቷል፤ እስካሁን 48 የአፍሪካ ሀገራት የግብይት ታሪፍ አቅርበዋል:: ኢትዮጵያ የግብይት ታሪፍ ያቀረበችው ባሳለፍነው ወር ነው:: ያቀረብነው የግብይት ታሪፍም በአፍሪካ የንግድ ሚኒስትሮች ምክር ቤት ተቀባይነት አግኝቷል ብለዋል::

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ ኢትዮጵያ በጥናት ላይ በመመስረት ለተቀባይ ሀገራት እያንዳንዱን ምርት የምትሸጥበትን የዋጋ ተመን አቅርባ ስምምነት ላይ ደርሳለች:: ከሌሎች ሀገራት ወደ ኢትዮጵያ የሚመጡ ምርቶች ዋጋ ደግሞ ድርድር እየተደረገበት ይገኛል::

በአፍሪካ ነጻ የንግድ ገበያ ማዕቀፍ 10 ሀገራት የሙከራ ትግበራውን ጀምረዋል ያሉት ሚኒስትሩ፤ “እኛም ምርቶችን ከለየንና ሀገራትን ከመረጥን በኋላ በጥቂት ወራት ውስጥ የሙከራ ንግድ እንጀምራለን” ሲሉ ተናግረዋል::

አክለውም፤ በቅርብ ጊዜ ውስጥ አንድ ነጥብ ሦስት ቢሊዮን ሕዝብ ያለውን ሰፊውን የአፍሪካ ገበያ የኢትዮጵያ አየር መንገድንና ሌሎችንም የሎጂስቲክስ አውታሮች ተጠቅመን በምርቶቻችን ለመድረስ ትልቅ እንቅስቃሴ እያደረግን ነው ብለዋል::

ኢትዮጵያ ከጎረቤት ሀገራት ጋር ጤናማ የንግድ ግንኙነት እንዳላት የጠቀሱት ሚኒስትሩ፣ ከጎረቤት ሀገራት ጋር የተፈረሙ ነባር የንግድ ስምምነቶችን የማሻሻል ሥራ እየተሠራ መሆኑን ገልጸው፣ ከጫት ግብይት ጋር በተያያዘ ከጂቡቲ ጋር በቅርቡ አዲስ ስምምነት ላይ መደረሱን በአብነት አንስተዋል::

ጫት ወደ ጂቡቲ የሚላከው ደረጃ ወጥቶለት አንደኛ እና ሁለተኛ ደረጃ እየተባለ መሆኑን የጠቀሱት ሚኒስትሩ፤ “ከ43 ዓመታት በፊት የተወሰነ የመሸጫ ዋጋው ሳይቀየር ቆይቶ በቅርቡ በሁለቱ ሀገራት የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤቶች በኩል በተደረገ ድርድር ስምምነት ላይ ተደርሶ የዋጋ ማስተካከያ ማድረግ ተችሏል” ብለዋል::

ሚኒስትሩ ኢትዮጵያና ኬንያ ከድንበር ንግድ ጋር በተያያዘ የየራሳቸው ፍላጎቶች ስላሏቸው ድርድር እያካሄዱ እንደሚገኙ ገልጸዋል:: ኢትዮጵያ ወደ ውጭ የምትልካቸው ምርቶች በድንበር አካባቢ ግብይት እንዲካሄድባቸውና ለኮንትሮባንድ ግብዓት እንዲሆኑ እንደማትፈልግ ጠቅሰው፣ ኬንያ በበኩሏ ወደ ኢትዮጵያ መላክ ከምትፈልጋቸው የምርት አይነቶች አንዳንዶቹ በኢትዮጵያ የማይፈለጉ በመሆናቸው ድርድሩ ቀጥሏል ብለዋል::

ከደቡብ ሱዳን ጋር ላለው የንግድ ልውውጥም አዲስ የድንበር ንግድ መመሪያ ተዘጋጅቶ ፍትህ ሚኒስቴር አስተያየት እንደሰጠበት አመላክተው፤ በቅርቡ ሲጸድቅ የነበረውን ስምምነት የሚያሻሽል ስለሚሆን የንግድ ግንኙነታችንን ይበልጥ የሚያሳድገው ይሆናል ብለዋል::

# ኢትዮጵያና እንግሊዝ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የመግባቢያ ስምምነቱን በሚመለከት ከእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና ከፓርላማቸው ጋር ውይይት ተደርጓል ያሉት አምባሳደሩ፤ በዚህም የሁለቱን ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ወደ ስልታዊ አጋርነት ለማሳደግ ተስማምተናል ብለዋል:: የሁለቱ ሀገራት ትብብር እና ግንኙነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተጠናከረ መምጣቱንም ተናግረዋል።

የመግባቢያ ሰነዱ መፈረም በትምህርት፣ በጤና፣ በማኑፋክቸሪንግ፣ በአግሮ ፕሮሰሲንግ፣ በኢንቨስትመንት፣ በንግድ፣ በሕዝብ ለሕዝብ ትስስር እና በሌሎች ዘርፎች በሁለቱ ሀገራት መካከል ያለውን ስትራቴጂያዊ ትብብር ለማጠናከር እንደሚረዳም አብራርተዋል።

በተጨማሪም ክፍተቶችን በመገምገም ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነቶችን የበለጠ ለማስፋት አስተዋፅኦ ያደርጋል ነው ያሉት አምባሳደር ተፈሪ።

እንደ አምባሳደር ተፈሪ ገለፃ፤ የሰሜን ኢትዮጵያን ግጭት ተከትሎ እንግሊዝ ማዕቀብ አልጣለችም። ይህም የሁለቱን ሀገራት ግንኙነት ይበልጥ እንዲጠናከር እድል ፈጥሯል። የእንግሊዝ መንግሥት በቅርቡ ለኢትዮጵያ እና ለሌሎች ሀገራት የነፃ ታሪፍ እና የታክስ ዕድልም ጀምሯል።

ኢትዮጵያ በግብርና፣ በማኑፋክቸሪንግ እና በአግሮ ፕሮሰሲንግ ላይ ጠንካራ ሥራ እየሠራች በመሆኑ በእንግሊዝ የወጪ ንግድ ገበያ ላይ ጠንካራ ተሳትፎ እንደምታደርግም ገልጸዋል።

የእንግሊዝ መንግሥት በ2024 የልማት ርዳታውን ከ80 ሚሊዮን ዩሮ ወደ 200 ሚሊዮን ለማሳደግ ቃል ገብቷል ያሉት አምባሳደር ተፈሪ፤ ይህ የሚያሳየው የሁለቱ ሀገራት ግንኙነት እያደገ መምጣቱን ነው ሲሉ ገልጸዋል።

በአዲስ አበባ በተካሄደው የኢንቨስትመንት ኮንፈረንስ ከመላው ዓለም ከመጡት ባለሀብቶች ውስጥ 20 በመቶዎቹ የእንግሊዝ ባለሀብቶች መሆናቸውን ገልጸው፤ በተጨማሪም የእንግሊዝ ባለሀብቶች በማዕድን፣ በኢነርጂ፣ በፋርማሲዩቲካል እና በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ኢንቨስት ለማድረግ ፍላጎት እያሳዩ ነው ብለዋል።

# “ከሶማሊላንድ ጋር የተደረገው ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ብቻ ሳይሆን ባለው የመልከዓ ምድር አቀማመጥ ስሌት በርካታ ጥቅሞች ያስገኝላታል::

የሶማሊላንድ መልከዓ ምድር አቀማመጥ በዓለም ኢኮኖሚ፣ ፖለቲካና ማሕበራዊ እንቅስቃሴ በብዙ መልኩ ወሳኝ ነው ያሉት አቶ ሌንጮ፤ ኢትዮጵያ ለኢኮኖሚዋ እድገት ብሎም ኃያላን የሚፈነጩበትና የሽብርተኞች እንቅስቃሴ የሚበዛበት ይህንን የቀይ ባሕር ቀጣና ባለድርሻ መሆን ለሀገሪቱ ሁለንተናዊ ደህንነት ወሳኝ ጉዳይ መሆኑን ተናግረዋል::

በአሁኑ ጊዜ አንዳንድ ወገኖች በስምምነቱ ዙሪያ የሚወረውሯቸው አሉታዊ አስተያየቶችና የሚያሰሙት ጩኸት ጊዜያዊ ነኄ ያሉት አቶ ሌንጮ፤ በኢትዮጵያ በኩል ግን በሳል የዲፕሎማሲ እንቅስቃሴ በተጠናከረ መልኩ ማካሄድና በተለይ የኢትዮጵያና የሶማሊላንድ ሕዝቦች የጉዳዩ ባለቤት ለማድረግ ሰፊ ሥራ መሠራት እንዳለበት ጠቁመዋል::

የሶማሊላንድ ሕዝብ ሶማሊያ ጋር አንድነት በፍጠሩ ዘግናኝ በደል ብሎም የዘር ማጽዳት ሰቆቃ ያስተናገደ በተቃራኒው ከኢትዮጵያ ጋር ወዳጅነቱ የተጠናከረ መሆኑን በደንብ ማሳየት ይጠቅማል ብለዋል::

ሶማሊላንድ እ.ኤ.አ በ1960 ከእንግሊዝ ቅኝ ግዛት ነጻ መውጣቷን ካወጀች ከጥቂት ቀናት በኋላ በራሷ ፍላጎት ሶማሊያን መቀላቀሏን ያወሱት አቶ ሌንጮ፤ ነገር ግን የታሰበው አንድነት ቀርቶ በአምባገነኑ የወቅቱ የሶማሊያ መንግሥት በዚያድባሬ ከፍተኛ በደልና የዘር ፍጅት ስለተፈጸመበት በ1991 ወደ ነበሩበት ተመልሰው በሕዝበ ውሳኔ የራሷን መንግሥት መምረጥ መቻሏን አውስተዋል::

እንደ አቶ ሌንጮ ማብራሪያ፣ የባሕር በር የማግኘት ጉዳይ ከታሪካዊ ስኬት በላይ ታሪካዊ ጠላትነትም አፍጦ የሚገለጥበት ይሆናል:: ሶማሊያ ከኢትዮጵያ ጋር በይደር የመጣውን ታሪካዊ ልዩነት ለማጉላት ለጊዜው ትፍጨረጨራለች:: በተመሳሳይ መልኩ የኢትዮጵያ መልካም ነገር የማይጥማትና በታሪክ ሁሌም ጠላት መስላ የምትታይ ግብጽ የጠላትነት ካርድ ለመሳብ አጋጣሚዎች ሁሉ ትጠቀማለች:: የተወሰኑ ዓረብ ሀገራት እንደ ግድቡ የሶማሊያና የግብጽን ጩኸት ሊያስተጋቡ ይችላሉ::

ሆኖም ግን ኢትዮጵያ የባሕር በር በማጣት የከፈለችው መስዋእት ከፍተኛ በመሆኑ የሚመጣው ማንኛውም ተጽእኖ ከምታገኘው ጥቅም ጋር ስለማይነጻጸር ስምምነቱን እውን ከማድረግ ለሰከንድ እንኳ ወደኋላ ማለት የለባትም ያሉት አቶ ሌንጮ፤ በተለይ ከተባበሩት ዓረብ ኢምሬትስ ጋር እንደተፈጠረው መልካም ወዳጅነት ከቀሪዎቹ ዓረብ ሀገራት ጋር መልካም ግንኙነት መፍጠር ጠቃሚ መሆኑን አስገንዝበዋል::

# የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

መርቀው ከፍተውታል።

ደጋሾቹ አንጋፋዎቹ ተቋማት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርና የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ናቸው። አውደ ርዕዩን ለእይታ ለማብቃት ከስድስት ወራት በላይ ደፋ ቀና ብለዋል። ገና ከበር ሲገባ ብዙ እንደተደከመበት ይናገራል። ከንግሥተ ሳባ ታሪክ ጀምሮ እስከ መጪው ዘመን ዲፕሎማሲ በሰፊው ቀርቧል። በጽሁፍ፣ በቪዲዮና ፎቶግራፍ ተቀናጅቶ መቅረቡ ታይቶ እንዳይጠገብና እጅጉን አስተማሪ እንዲሆን አድርጎታል።

በውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት ከፍተኛ ተመራማሪና የኤዥያን ፓስፊክ ጥናት ዳይሬክተር ጀኔራል እና የአውደ ርዕዩ አዘጋጅ ኮሚቴ አባል አንተነህ ጌታቸው (ዶ/ር) አውደ ርዕዩን አስመልክተው እንደሚናገሩት ተቋማዊ የሆነ የውጭ ግንኙነት ሥራና ዲፕሎማሲ የተጀመረበት የ 116 ዓመት ታሪክ እና ጥንታዊ ዲፕሎማሲ ከንግሥተ ሳባ እስከ መጪው ትውልድ ዲፕሎማሲ በሰፊው ቀርቦበታል::

በዲፕሎማሲ ሥራ በርካታ ታሪኮች ተመዝግበዋል። በታሪኩም ብዙ ውጣ ውረድ፣ መውደቅ መነሳትና ስኬት ነበር የሚሉት ዶክተር አንተነህ፤ ይሁንና የተሠራውን ነገር በአግባቡ ያለማወቅ፣ ባወቅነውም ልክ ያለመጠቀምና በአግባቡ መዝግበን ለቀጣይ ትውልድ የማስተላለፍ ችግር አለ። ይህንን ታሳቢ በማድረግ የትናንት፣ የዛሬንና የነገን ዲፕሎማሲ በሶስት የጊዜ ምዕራፍ ተሰንዶ ለተተኪ ዲፕሎማቶች ስንቅ በሚሆን መልኩ ቀርቧል ብለዋል።

አውደ ርዕዩ ስድስት ክፍሎች አሉት። ከውጭ ግንኙነትና ዲፕሎማሲ አንጻር በየዘመኑ የተሠራው ከንግሥተ ሳባ ጀምሮ እስከ ዓድዋ ድል ድረስ በመጀመሪያው ምዕራፍ ቀርቧል።

የዘመናዊ ዲፕሎማሲ በኢትዮጵያ የሚለው በሁለተኛው ክፍል ቀርቧል። ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ከተቋቋመ ጀምሮ ያለውን የ 116 ዓመት አሠራር፣ አደረጃጀት፣ ሀገሪቱ የምትከተለውን የዲፕሎማሲ ሥራ በስፋት ያስረዳል።

ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በተጨማሪ ቱሪዝም ሚኒስቴር፣ መከላከያ ሚኒስቴር፣ አየር መንገድ እና ሌሎች ተቋማት በሰላም ማስከበር፣ በቅርስ ማስመለስ፣ በስፖርትና በጤና ለዲፕሎማሲ ሥራ ያበረከቱት አስተዋጽኦና አሁንም እየሠሩት ያለውም ለአይን በሚማርክ ሁኔታ እየተጎበኘ ነው።

ኢትዮጵያ መስራች አባል የሆነችበት የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት፣ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ፣ ኢጋድ ፣ በቅርቡ አባል የሆነችበት ብሪክስን ያካተተ የባለብዙ ወገን ዲፕሎማሲ በሶስተኛው ክፍል እንደሚገኝ ያስረዳሉ።

በጋራ በመልማት፣ በጋራ በማደግ፣ በጋራ ደህንነት፣ በቀጣናዊ ትስስር እና የዓለም ሀገራት አጀንዳ በሆነው የአየር ንብረት ለውጥ የኢትዮጵያ አቋም በስፋት ተንጸባርቋል።

ዲፕሎማሲያችን ዛሬ አራተኛው ክፍል ሲሆን የአውደ ርዕዩን ሰፊ ድርሻ ይዟል። ትኩረቱን በድህረ ለውጡ ዲፕሎማሲ ቢያደርግም እየተሠሩ ያሉ ሥራዎች ከትናንት መነሻ ታሪካቸው ጋር ተቀናጅተው መቅረባቸውን ይገልጻሉ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ወደሥልጣን ሲመጡ ስለሚከተሉት የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ በፓርላማ ባደረጉት ንግግር መግለጻቸውን ያስታወሱት ዶክተር አንተነህ፤ በቃላቸው መሠረት ያከናወኑት ቀጣናዊ ትስስርን የማጠናከር፣ ከጎረቤቶች ጋር በጋራ የመልማት፣ የዜጋ ተኮር ዲፕሎማሲ፣ የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ፣ የሁለትዮሽ እና በባለብዙ ወገን መድረክ ግንኙነት እንዲሁም የአረንጓዴ ዐሻራ፣ የህዳሴ ግድብ፣ የኃይል ሽያጭና ሌሎች ውጤታማ ሥራዎችን በተግባር ማሳየት ተችሏል ብለዋል።

በመጨረሻው ክፍል የቀረበው የመጪው ዘመን ዲፕሎማሲ መሆኑን ገልጸው፤ ለቀጣይ የውጭ ግንኙነትና የዲፕሎማሲ ሥራ መጠናከር የዲጂታል ዲፕሎማሲንና የሰው ሰራሽ አስተውሎትን ለትውልዱ ለማሳወቅ መቅረቡን ይናገራሉ።

በመጪው ዘመን የዲፕሎማሲና የተቋማት መረጃ በዘመናዊ መልኩ የተደራጀ እንዲሆን ለማድረግ፣ እውቀት መር ጥናትና ምርምሮችን እና የሀገሪቱን ብሔራዊ ጥቅምና ገጽታ ለመገንባት ቴክኖሎጂን መጠቀም ተገቢ ነው። ለዚህ ደግሞ ቴክኖሎጂን በአግባቡ የሚጠቀም ዲፕሎማት ማፍራት እንደሚገባ ያስረዳል።

በአጠቃላይ የአውደ ርዕዩ ዓላማ በውጭ ግንኙነትና በዲፕሎማሲው ዙሪያ የተሠሩትን ሥራዎች ለትውልዱ ለማሳወቅ ሲሆን፤ የተጀመረው አውደ ርዕይ ትልቅ የታሪክ ሰነድ በመሆኑ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቋሚ ኤግዚቢሽን እንዲኖረው ይሠራል ብለዋል።

በየዘመኑ የተሠሩ በጎ የዲፕሎማሲ ሥራዎችን መጠበቅ፣ ዲፕሎማቶችን ማክበር፣ ያጋጠማቸው ፈተና ነገ እንዳይደገም መመሪያ ማድረግ፣ አጨቃጫቂ ታሪኮችን ለታሪክ አጥኚዎች መተው፣ ብሔራዊ ጥቅምንና ፖለቲካን መለየት፣ የውስጥ ችግሮችን መፍታት ከትውልዱ ይጠበቃል ብለዋል።

አውደ ርዕዩን ከጎበኙት መካከል የመከላከያ ቅርስ ጥበቃ፣ ጥናትና አስተዳደር ዳይሬክተር ብርጋዴር ጀነራል ደሳለኝ ዳቾ እንደሚሉት፤ በዲፕሎማሲ ሳምንት አውደ ርዕይ የቀረቡት የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት፣ የአረንጓዴ ዐሻራና የህዳሴ ግድብ ዲፕሎማሲዎች አስተማሪ ናቸው።

የዲፕሎማሲ ሳምንት አውደርዕዩ ኢትዮጵያ የረጅም ዘመን የዲፕሎማሲ ታሪክ ባለቤት መሆኗን እና ከንግሥተ ሳባ ጀምሮ እስካሁን ድረስ ያለውን የዲፕሎማሲ ውጣ ውረድ በፎቶ፣ በቪዲዮና በጹሁፍ ተቀናጅቶ ቀርቦ መመልከት ችለናል ብለዋል።

ያለፉት መሪዎች አስጠብቀው ያቆዩትን የዲፕሎማሲ ሥራ ወደፊት ለማስቀጠል የአሁኑ ትውልድ ኃላፊነቱን ሊወጣ እንደሚገባም አስታውቀዋል።

ኤግዚቢሽኑን ሲጎበኙ ያገኘናቸው አቶ ተገኝ አለማየሁ በበኩላቸው አውደ ርዕዩ የሀገሪቱን ታሪክ የሚያሳውቅ መሆኑን ገልጸው፤ ሁሉም ኢትዮጵያውያን መረዳት እንዲችሉ በሌሎች የሀገሪቱ ክፍሎችም ሊዘጋጅ እንደሚገባ ጠቁመዋል።

ቀጣይ በሀገሪቱ በሚኖረው ዲፕሎማሲ የሁሉም ማህበረሰብ አስተዋጽኦ ሊኖርበት ይገባል ያሉት አቶ ተገኝ፤ በዚህም ኢኮኖሚን በማሳደግ፣ ማህበራዊ ግንኙነቶችን በማጠናከር እና በሌሎች ሥራዎች ላይ ዐሻራቸውን ሊያሳርፉ ይገባል ብለዋል።

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## በዲጂታል ቴክኖሎጂው በፍጥነት ለመጓዝ

**አስናቀ ፀጋዬ**

ግሎባላይዜሽን /ሉላዊነት/ አድማሱን አስፍቷል፤ ዓለም የአንድ መንደር ያህል እየሆነች ትገኛለች። አንዱ የዓለም ክፍል የሚፈልጋቸው ነገሮች ርቀት ሳይገድባቸው በፍጥነት የሚደርሱበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ለእዚህ መቀራረብ ደግሞ ዲጂታል ቴክኖሎጂ ትልቁን ስፍራ ይይዛል።

ሰዎች ይህንን ቴክኖሎጂ ተጠቅመው መረጃዎችን በቀላሉ መለዋወጥ፣ ስራቸውን ማቀላጠፍ፣ ንግዳቸውን ማጧጧፍና ሌሎችንም ተግባራትን እየፈጸሙ ይገኛሉ። ዛሬ በረቀቁ የዲጂታል ቴክኖሎጂ መንገዶች በመጠቀም ንግድን ማቀላጠፍ፣ መማርና ማስተማር፣ ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ የፋይናንስ ስርዓቶችን መቆጣጠር፣ ሕዝብን መምራት፣ ማገልገል፣ ክፍያዎችን መፈጸም፣ ወዘተ. ቀላል ሆኗል።

ለሀገራችን ይህ ክስተት የቅርብ ጊዜ ቢሆንም፣ በዚህ የዲጂታል ቴክኖሎጂ አማካይነት ብዙ ነገሮች እየተፈጸሙ ይገኛሉ። በሀገሪቱ ከጥቂት ዓመታት በፊት የዘርፉን የፈጠራ ስራዎች ለማበረታትና የስራ እድል ለመፍጠር ትልቅ ትኩረት ተሰጥቶት ወደ ስራ ተገብቷል። በተለይ ዲጂታል ኢኮኖሚ በመገንባት ረገድ ብዙ እየተሰራ ይገኛሉ።

ሀገሪቱ ለዘርፉ ትልቅ ትኩረት ሰጥታለች። ሀገሪቱ በአገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያው ትኩረት ከሰጠቻቸው አምስት የምጣኔ ሀብቱ ዘርፎች አንዱ ይሄው የኢንፎርሜሽንና ቴክኖሎጂ ዘርፍ ነው። ይህን ተከትሎም በዘርፉ በርካታ ተግባሮች እየተከናወኑ ናቸው።

ዲጂታል ኢኮኖሚ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለመቅረፍ፣ የንግድ አገልግሎትን በዘመናዊ መልኩ ለማቀላጠፍ፣ የአገልግሎት ጥራትን ለመጨመር፣ ዘላቂ እድገት ለማስመዝገብ ብሎም ዜጎች በሁሉም መስኮች ክህሎት እንዲያዳብሩ ለማድረግ ፋይዳ የጎላ እንደሆነ ታምኖበታል።

ከዚህ አኳያ ኢትዮጵያ በ2025 የዲጂታል ኢኮኖሚን እውን ለማድረግ የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ስትራቴጂ ነድፋ እየሰራች ትገኛለች። ስትራቴጂውም የተለያዩ የትኩረት አቅጣጫዎችን የያዘ ሲሆን፤ ከነዚህ ውስጥ የዲጂታል ኢኮኖሚውን ለማቀላጠፍ የሚረዱ መሰረተ ልማቶችን መገንባት፣ የዲጂታል ፕላትፎርሞችን መመስረትና የዲጂታል ስነ ምህዳር ልማትን ማስፋፋት የሚሉት ይገኙበታል።

በኢትዮጵያ የኢኮኖሚ እድገቱን የሚመጥን የዲጂታል ኢኮኖሚ ስርዓት መገንባትና በአለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆነ ኢኮኖሚ እንዲኖር አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበት እየተሰራ ቢሆንም፣ በማህበረሰቡ በኩል ያለው የዲጂታል ቴክኖሎጂ እውቀትና የግንዛቤ ደረጃ ዝቅተኛ መሆን አሁንም በዚህ ዘርፍ ለማደግ በሚደረገው ጥረት ውስጥ እንደ አንድ ተግዳሮት ሆኖ ይጠቀሳል።

አቶ ዳንኤል በቀለ የአሸዋ ቴክኖሎሎጂ መስራችና ዋና ስራ አስኪያጅ ነው፤ በሙያውም ሶፍትዌር ኢንጂነር ነው። እሱ እንደሚለው፤ ድርጅቱ አሸዋ ቴክኖሎጂ በቅርቡ ‹‹ናህቢ›› የተሰኘ የድረገፅ መገንቢያ መሳሪያ ይፋ አድርጓል። የድረ ገፅ መገንቢያ መሳሪያ ድር ተኮር/web based/ መተግበሪያ ሲሆን፣ ማንኛውም የመንግሥትም የሆነ የግል ተቋም ድረ ገፅ መስራት ቢፈልግ ጥልቅ እውቀት እንዲኖረው ሳይጠበቅበት በፍጥነትና በአስተማማኝ ሁኔታ ለመስራት ያስችለዋል።

በኢትዮጵያ ውስጥ እስካሁን ባለው ሂደት በዚህ ደረጃ የተዘጋጀ የድረ ገፅ መገንቢያ መሳሪያ የለም። ይሁንና ይህ ቴክኖሎጂ በሌላው አለም የሚታወቅና የተለመደ ነው። ለአብነትም ዎርድ ፕረስ፣ ዊክስ፣ ሾፕ ፋይል እና የመሳሰሉትን የድረ ገፅ መገንቢያዎች መጥቀስ ይቻላል።

አሸዋ ቴክኖሎጂ ይዞት የመጣው ስርዓት በዚህ ዘርፍ ላይ ያሉ ዓለም አቀፍ ተቋማት የያዟቸውን ቴክኖሎጂ ነው። ከዚህ አንፃር ቴክኖሎጂው ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለአፍሪካ ገበያም ጭምር ይተርፋል። ድረ ገፅ መገንቢያው የተሰራው በአፍሪካና በመላው ዓለም ካሉ ተመሳሳይ የድረ ገፅ መገንቢያ ቴክኖሎጂዎች ጋር ተወዳዳሪ መሆኑን ከግምት ውስጥ በማስገባት ሲሆን፤ ከሁሉም በላይ ለኢትዮጵያ ገበያ እጅግ ጠቃሚ መሳሪያ ነው።

**ኢትዮጵያ ደግሞ ዓለም የደረሰበት የቴክኖሎጂ ደረጃ ላይ ለመድረስ አሁንም ገና ብዙ መስራት ይጠበቅባታል። ከቴክኖሎጂው ጋር ያለመግባባትና ቴክኖሎጂው በደረሰበት ደረጃ ልክ አውቆ ወደፊት የመጓዝ ችግሮች ይታያሉ**

አቶ ዳንኤል እንደሚሉት፤ የዲጂታላይዜሽን ዘመን እንደመሆኑ ድርጅትና ቢዝነስ ያላቸው ሰዎች፣ ባለሙያዎች የመንግሥትና የግል ተቋማት በዚህ የድረ ገፅ መገንቢያ አማካኝነት በቀላሉ የራሳቸውን ድረ ገፅ ገንብተው ቢዝነሳቸውን፣ ንግዳቸውንና ሌሎችንም የሚፈልጓቸውን ነገሮች ማቀላጠፍ ይችላሉ። ለምሳሌ አንድ ባለሙያ እውቀቱን መሸጥ ቢፈልግ በዓለም አቀፍ ዙሪያ ካሉ ባለሙያዎች ጋር ተወዳድሮ በኦንላይን ራሱን ለገበያ እንዲያቀርብና ከበርካታ ደንበኞች ጋር የመገናኘትን እድል ድረ ገፅ መገንቢያው ይፈጥርለታል፤ ብራንዱን/መለያውን/ ይገነባለታል፤ ተአማኒነቱን ይጨምርለታል። ደምበኞች ስለ አንድ ድርጅት አድራሻና መረጃዎች ቢፈልጉ በቀላሉ ማግኘት ያስችላቸዋል። በራስ ድረገፅ አማካኝነት በኦን ላይን ምርቶችን ለመሸጥም ያግዛል። የድረ ገፅ መገንቢያው ከዓለም ጋር ለመራመድ እድል የሚሰጥም ጭምር ነው ።

በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ከ34 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ሰዎች የኢንተርኔት ተጠቃሚዎች ናቸው ተብሎ ይታሰባል። ከዚህ አንፃር እያንዳንዱ የመንግሥትም ሆነ የግል ድርጅት ብሎም ግለሰቦችና የቢዝነስ ሰዎች ምርቶቻቸውን በዲጂታል ወይስ በተለመደው መንገድ እያስተዋወቁ ስለመሆናቸው ራሳቸውን መጠየቅ ይኖርባቸዋል። ከዚህ አንፃር የድረ ገፅ መገንቢያ በሀገር ውስጥ ብቻ የታጠረ ባለመሆኑና ለአለምም ጭምር ክፍት በመሆኑ እነዚህ አካላት ምርቶቻቸውን በዲጂታል መንገድ የሚያስተዋውቁ ከሆነ ብራንዳቸውን/መለያቸውን/ ከፍለማድረግ እድል ይሰጣል።

አቶ ዳንኤል እንደሚያብራሩት፤ ዓለም በቴክኖሎጂ ፈጥኗል። ኢትዮጵያ ደግሞ ዓለም የደረሰበት የቴክኖሎጂ ደረጃ ላይ ለመድረስ አሁንም ገና ብዙ መስራት ይጠበቅባታል። ከቴክኖሎጂው ጋር ያለመግባባትና ቴክኖሎጂው በደረሰበት ደረጃ ልክ አውቆ ወደፊት የመጓዝ ችግሮች ይታያሉ። እንደዛም ሆኖ ፈጥነው የመጡ የውጪ ሀገር ቴክኖሎጂዎችን ለመጠቀም ‹‹ፔን ፓል›› እና ‹‹ማስተር ካርድ›› የተሰኙት ደርጅቶች የውጪ ምንዛሪን ይጠይቃሉ። በዚህም ምክንያት በርካታ ወጣቶች፣ የፈጠራ ስራ ባለሙያዎችና ድርጅቶች የድረ ገፅ ባለቤት እንዳይሆኑ ችግር ፈጥሮባቸዋል። በእዚህ አይነት ሁኔታ እነዚህን አካላት የቴክኖሎጂ ተደራሽ ማድረግም ቀላል አይደለም።

አሸዋ ቴክኖሎጂ እንደ አንድ የቴክኖሎጂ ድርጅት እየሰራ ያለው ቴክኖሎጂውን ለሕብረተሰቡ በሚፈለገው ልክ ተደራሽ ማድረግ ላይ ነው። ከዚሁ ጎን ለጎን በዲጂታል እውቀትና አጠቃቀም ዙሪያ ያለውን ክፍተት ለመሙላት ከሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ጋር የግንዛቤ ፈጠራ ስራዎችን ይሰራል፤ ውይይቶችንም ያደርጋል። በተመሳሳይ ከሌሎች አጋር ድርጅቶችና በዘርፉ ካሉ ባለሙያዎች ጋር በትብብር እየሰራ ዘርፉን ለማሳደግ ጥረት እያደረገ ይገኛል።

እንደ ሌሎች ዘርፎች ሁሉ ዲጂታል ቴክኖሎጂው በርካታ ስራዎች ሊሰሩበት የሚችል ሰፊ ዘርፍ መሆኑን ጠቅሰው፣ ማሕበረሰቡ ቴክኖሎጂው ገብቶት እንዲጠቀምበት ብቻ ሳይሆን በይበልጥ ሕይወቱንም የሚቀይርበት እድል የሚሰጠው መሆኑን ማሳየት ያስፈልጋል ይላሉ፤ ለእዚህ ደግሞ ቴክኖሎጂውን አስመልክቶ ሕብረተሰቡን ማስተማርና ግንዛቤ ማስጨበጥ ላይ መስራት እንደሚገባ አመልክተዋል።

‹‹በርካታ ሰዎች ድረ ገፅ አለን ቢሉም የድረ ገፅን ጥቅም በሚገባ ስለማያውቁ ድረ ገፅ እንዳላቸው እንኳን አይሰማቸውም›› ሲል ገልጾ፣ አብዛኛዎቹ ግለሰቦች የሚያውቁት ድረ ገፃቸውን እስከሚያሰሩበት ድረስ ያለውን ደረጃ እንጂ፣ ድረ ገፁ ከዛ በኋላ ይዞት ሊመጣ የሚችለውን በረከት፣ ሊያመጣ የሚችለውን ውጤትና ምን ያህል ሕይወት ቀያሪ እንደሆነ በቅጡ አይረዱም ይላል። ስለዚህ ይህንንም ጭምር ለሁሉም የሕብረተሰብ ክፍል ማስገንዘብ፣ የማሰልጠንና የማስተዋወቅ ስራዎች በድርጅቱ በኩል እየተሰሩ ይገኛሉ።

በአሁኑ ጊዜ መንግሥት የመንግሥት ተቋማትን ‹‹አውቶሜት›› የማድረግ፣ በቴክኖሎጂ የማዘመን፣ በቴክኖሎጂ እንዲመሩና አገልግሎቶችን ቀልጣፋና ምቹ የማድረግ ስራዎችን እያከናወነ ይገኛል። ይህም አበረታችና ይበል የሚያሰኝ ተግባር ነው። ነገር ግን ከዚህ ተግባር በተጨማሪ ድርጅቱ ለማሕበረሰቡ የዲጂታል መፍትሄ አቅራቢ መሆን ይፈልጋል። አንድ ተቋም ወይም ግለሰብ ምንም አይነት መተግበሪያና ድረ ገፅ ቢፈልግ ድረ ገፅ የማበልፀግ ስራ ይሰራል፤ ቴክኖሎጂውን ተደራሽ ለማድረግም ይተጋል። ማሕበረሰቡ ወደዲጂታል ቴክኖሎጂ መሄድ ፈልጎ ችግሮች ሳይገድቡት መስራት የሚችልበትን መድረክ ድርጅቱ ፈጥሯል። ይህ አይነቱ አገልግሎት በአሸዋ ቴክኖሎጂም ይሁን በሌሎች መሰል የቴክኖሎጂ ድርጅቶች በበዛ ቁጥር ደግሞ ዲጂታል ኢትዮጵያን እውን ማድረግ ይቻላል።

በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ረዳት ፕሮፌሰርና የሶፍትዌር ኢንጂነሪንግ ትምህርት ክፍል ኃላፊ ዶክተር ለምለም ካሳዬ፤ በዚህ ትምህርት ዘርፍ ያሉ ተማሪዎች የቴክኖሎጂ ፕሮጀክቶችን እንደሚሰሩ ጠቅሰው፣ ለዲጂታላይዜሽንም እጅግ የቀረቡ መሆናቸውን ይናገራሉ። የሚያከናውኗቸው ፕሮጀክቶች መደርደሪያ ላይ ከመቀመጥ ውጪ ስራ ላይ ውለው ውጤት እያመጡ አይደሉም ሲሉ ዶክተር ለምለም ይናገራሉ።

አሸዋ ቴክኖሎጂ ስራ ላይ ያዋለው ‹‹ነሃቢ›› የተሰኘው ድረ ገፅ መገንቢያ በዲጂታል ቴክኖሎጂው ዘርፍ ትልቅ እምርታ የታየበት ነው ብለዋል። ለሀገርም ሆነ ለወጣቱ የስራ እድል ፈጠራ አስተዋፅኦው የጎላ መሆኑን ጠቁመው፣ በተለይ በዚህ ዲጂታል ቴክኖሎጂ ዘርፍ ለሚንቀሳቀሱ ወጣቶች ትልቅ መነቃቃትን እንደሚፈጥርም ጠቁመዋል።

ዶክተር ለምለም እንደተናገሩት፤ ሕብረተሰቡ የተለያዩ የቴክኖሎጂ ሃብቶች እጁ ላይ አሉ። ስልክ፣ ታብሌት፣ ላፕቶፕ፣ ዴስክቶፕና ሌሎችም የቴክኖሎጂ ውጤቶች በሕዝብ እጅ ውስጥ ገብተዋል። የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ (የአይ ሲ ቲ) ቴክኖሎጂም የዛኑ ያህል በፍጥነት አድጓል። ሆኖም ግን አሁን ባለው ሁኔታ አብዛኛው ሰው የቴክኖሎጂ ሀብቱን በሚገባ እየተጠቀመበት አይደለም።

ከዚህ አኳያ በቅድሚያ ትልቅ ስራ መሰራት ያለበት በዲጂታል ቴክኖሎጂ ዙሪያ ሰፊ የግንዛቤ ማስጨበጥ ነው ሲሉም ያስገነዝባሉ። በሕብረተሰቡ በዲጂታላይዜሽን ላይ ያለው አመለካከት እንዲጨምር ተጨማሪ ስራ መስራት እንደሚያስፈልግም ተናግረው፣ በዛው ልክ ደግሞ የቴሌኮም መሰረተ ልማት አሁን ሀገሪቱ በደረሰችበት ኢኮኖሚያዊ እድገት ልክ አብሮ ማደግ ይጠበቅበታል ብለዋል። የኢንተርኔት ዋጋ ክፍያ ፍትሃዊ ካልሆነም መስተካከል እንደሚኖርበት ነው ያስገነዘቡት።

እንደ ኃላፊዋ ማብራሪያ፤ በኢትዮጵያ በተለይ በዲጂታል መንገድ ንግድ ማካሄድ አሁን አሁን በመጠኑ ተጀመረ እንጂ ከዚህ በፊት አልተለመደም። ቻይናን ጨምሮ ሌሎች ሀገራት ግን አብዛኛውን ግብይታቸውን የሚፈፅሙት በዲጂታል ቴክኖሎጂ አማካኝነት ነው። በኢትዮጵያ ዲጂታል ቴክኖሎጂውን ለመጠቀም በሕብረተሰቡ በኩል ያለው ግንዛቤ አነስተኛ መሆን ቴክኖሎጂውን ለመጠቀም ካለው የእውቀት ክፍተት ጋር ተዳምሮ በዲጂታል ቴክኖሎጂው ብዙ ርቀት አልተሄደም።

ዶክተር ለምለም የፒ ኤች ዲ ዲግሪያቸውን የሰሩት በዋይርለስ ኮሙዩኒኬሽን መሆኑንም ጠቅሰው፣ በዋይርለስ ኮሙዩኒኬሽን ሕብረተሰቡ ምን ያህል ተጠቅሞበታል የሚለው መጠናት እንዳለበት ይጠቁማሉ። እነዚህን ገመድ አልባ የመግባቢያ መሳሪያዎች በምን ያህል ደረጃ ሕብረተሰቡ እየተጠቀመባቸው እንዳለ ብቻ ሳይሆን እነዚህ መሳሪያዎች የመጠቀም እውቀቱ ምን ያህል እንደሆነ ተጨማሪ ጥናት እንደሚያስፈልግ ይናገራሉ። “እንዴት መጠቀም እንደሚቻልም ተመሳሳይ ጥናት ማድረግ እንደሚገባና ይህን ማድረግ የሚቻል ከሆነ ወደ ዲጂታል ዓለም የምናደርገውን ግስጋሴ ማፋጠን እንችላለን” ይላሉ።

የዲጂታል ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ክፍተትና የግንዛቤ እጥረት ብቻ ሳይሆን ድህነትም ተጨማሪ ምክንያት መሆኑንም ዶክተር ለምለም ተናግረው፤ ዲጂታል ቴክኖሎጂውን የሚጠቀመው በአብዛኛው በከተማዎች አካባቢ የሚኖረው የሕብረተሰብ ክፍል መሆኑን ገልጸዋል። ቴክኖሎጂውን በተቀረው የኢትዮጵያ ክፍሎችም ተደራሽ ማድረግ እንደሚገባ ያመለክታሉ። ለዚህ ደግሞ ኢትዮጵያ ከድህነት መላቀቅ እንደሚገባት ይጠቁማሉ።

ዶክተር ለምለም እንደሚሉት፤ የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ የመንግሥትን ትኩረት አግኝቶ እየሰራ የሚገኝ ትልቅ ተቋም ነው። በኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ (አይ ሲቲ)፣ በዳታ፣ በሳይበር ሴኪዩሪቲ፣ በሶፍትዌር ቴክኖሎጂ የልህቀት ማእከላት አሉት። በዲጂታል ቴክኖሎጂም በርካታ ተሞክሮዎች አሉት።

በዚህ ረገድ አዳዲስ ነገሮችን መፍጠር የሚችሉና በዲጂታል ቴክኖሎጂ ዘርፍ ሀገሪቱ የምትፈልገውን መፍትሄ ሊያመጡ የሚችሉ ተማሪዎችንም ይዟል። ከዚህ አኳያ እንዲህ አይነቱን ሀብት በስፋት ጥቅም ላይ ማዋል የሚቻል ከሆነ የዲጂታል ቴክኖሎጂውን ወደፊት ማራመድ ይቻላል ።

# ወቅታዊ ትንታኔ

## ለፈጣንና ተከታታይ እድገት - የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ

**አስቴር ኤልያስ**

ኢትዮጵያ ከጊዜ ወደጊዜ በአፍሪካም ሆነ በዓለም አቀፍ መድረክ ተሰሚነቷ እየጎለበተ መጥቷል። በተለይም ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በዲፕሎማሲው መስክ እያስመዘገበች ያለው ስኬት ብዙዎቹ አገራት በራቸውን ያለአንዳች ማቅማማት እንዲከፍቱላትም ምክንያት ሆኗል።

አገሪቱ በአሁኑ ወቅት ትኩረት አድርጋ እየተንቀሳቀሰች ያለችው በኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ ላይ እንደሆነ ይታወቃል። ቀጥተኛ የውጭ ምንዛሬን በማምጣት እና ከዚህ ጎን ለጎን በአገር ውስጥ የሚከናወኑ የልማት ፕሮጀክቶችንም በመደገፍ የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲው አይነተኛ ሚና እየተጫወተ ይገኛል።

የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ ሲባል የራሱ መገለጫ እንዳለው በዘርፉ የተጻፉ መረጃዎች ያመለክታሉ። የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ ሲባል የንግድ ልውውጥን በማሳደግ፣ ኢንቨስትመንቶችን በማስተዋወቅ፣ በሁለትዮሽ እና በባለብዙ ወገን የንግድ ስምምነቶች ላይ ትብብርን እና የመሳሰሉትን በማከናወን የአገርን ኢኮኖሚ ለማሳደግ የሚደረግ አካሄድ ነው ሊባል ይችላል። የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ፣ በዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ጉዳዮች ላይ ብልጽግናን ለማጎልበት የሚያስችል ቀዳሚው ዲፕሎማሲ ሲሆን፣ በአሁኑ ወቅት በአብዛኞቹ የዓለም አገራት ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ እየሆነ መጥቷል።

የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ ዘርዘር ባለ መልኩ ሲታይ ደግሞ የመንግስትን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም የሚያራምድ ማንኛውም ዲፕሎማሲያዊ ተግባር ተብሎ ሊገለጽ እንደሚችል በዘርፉ የሰፈረው ማረጃ ያመላክታል። አንድ የተወሰነ የውጭ ፖሊሲ ዓላማን ለማሳካት የኢኮኖሚ ሀብቶችን የሚጠቀም ዲፕሎማሲንም ሊያካትት እንደሚችል ያስረዳል። በሌላ በኩል ደግሞ በነጠላ ትርጉሙ ሲታይ የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ የኤክስፖርት ማስተዋወቅ እና የውስጥ ኢንቨስትመንት ሲሆን፣ ይህ አንዳንዴ የንግድ ዲፕሎማሲ ሊባል እንደሚችልም ይገለጻል።

በዘርፉ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው፤ የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ ጠቀሜታው የንግድ እና የንግድ ኃይሉን በመጠቀም አገሮች እርስ በእርስ አዎንታዊ ግንኙነቶችን መፍጠር ማስቻሉ ነው። መተማመን እና መግባባት ላይ መድረስ፣ ለዕድገት እና ለልማት አዳዲስ ዕድሎችን መፍጠርም ሌላው ጠቀሜታው ነው። በመሰረቱ የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ ፖለቲካዊ ዓላማን ለማሳካት ኢኮኖሚያዊ መንገዶችን መጠቀም እንደማለት ነው።

የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ ዓላማዎች ከሆኑት መካከል ዋናው ትኩረት ማስተዋወቅ፣ የውጭ ንግድን፣ ኢንቨስትመንቶችን፣ ቴክኖሎጂን እና ቱሪስቶችን መሳብ ነው። የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ ከፖለቲካዊ፣ ህዝባዊ እና ሌሎች የዲፕሎማሲ ስራዎች ክፍሎች ጋር በቅርበት የሚገናኝም ነው።

ከኢፌዴሪ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው፤ የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲው የኢትዮጵያ ውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ዋነኛው አዕማድ መሆኑ ነው። በዚህም አገሪቱ የኢኮኖሚያዊ ጥቅሞቿን በዓለም አቀፍ ግንኙነት መድረክ ለማሳካት የምትችልባቸውን ልዩ ልዩ ተግባራት ስትከውን ቆይታለች። የውጭ መዋዕለ ነዋይ በሰፊው ለመሳብና ቀጥተኛ የውጭ ኢንቨስትመንት የማሳደግ የኢትዮጵያ ምርቶች ገበያ እንዲያገኙ ዋነኛ ግቧና መርህ አድርጋ ወደ ሥራ በመግባቷ ውጤት እያስመዘገበች መሆኑንም ያመለክታል።

እንደመረጃው ከሆነ፤ ይህን ለማሳካት ፖሊሲ ነድፎ ሳቢ እና አስቻይ ሁኔታዎችን የመፍጠር ሥራዎችም ተሰርተዋል። የግብር እፎይታ፣ ከቀረጥ ነፃ ፈቃድ እና ሌሎች መደላድሎችን የማዘጋጀት ጥረት ተደርጎ የውጭ ባለሃብቶች ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲያለሙ ስራዎች በመሠራታቸው በርካታ ኢንቨስተሮች በኢትዮጵያ በተለያዩ ዘርፎች ተሰማርተዋል። ይህ ምቹ ሁኔታ በዲፕሎማሲ ጥረት ታግዞ መልካም ውጤት ተገኝቶበታል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በዲፕሎማሲው መስክ የኢፌዴሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር ምስጋኑ አርጋ እና የቀድሞ ዲፕሎማትና የሰብዓዊ መብት ኮሚሽነር አምባሳደር ጥሩነህ ዜናን ባነጋገረበት ወቅት አምባሳደር ምስጋኑ እንዳሉት ኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲን ለአገራችን ልማት ዋነኛ የትኩረት አቅጣጫ በመሆኑ ትኩረት ተደርጎ እየተሰራበት ይገኛል። በአሁኑ ወቅት የፖለቲካ ዲፕሎማሲው የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲውን ማዕከል እንዲያደርግ በመሰራት ላይ እንደሆነም አስረድተዋል።



አምባሳደር ምስጋኑ አርጋ



ፎቶ - እዮብ ተፈራ

አምባሳደር ጥሩነህ ዜና

እርሳቸው እንደተናገሩት፤ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ ሠላምና የሀገር ውስጥ ልማትን በሚያረጋግጡ ጉዳዮች ላይ ትኩረት አድርጓል። በዲፕሎማሲው ዘርፍ ዋነኛ የትኩረት ማጠንጠኛ ከሆኑ ጉዳዮች መካከል የኢኮኖሚው ዲፕሎማሲ አንዱ ነው። በመሆኑም በዚህ ዲፕሎማሲ መስክ አዳዲስ የሥራ ስምምነቶች ተደርገዋል።

የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲው ተጨማሪ የቴክኒክ እና የቴክኖሎጂ ሽግግርን ማምጣት እንዳለበትም የሚናገሩት አምባሳደሩ፣ የሀገር ውስጥ የልማት ፖሊሲና ስትራቴጂዎች በውጭ ሀገራት የዲፕሎማሲ ግንኙነቶች እንዲታገዙ በማድረግ ልማትን ለማፋጠን ሰፊ ጥረት መደረጉን ገልጸዋል። የገበያ ተደራሽነትንም ለማሳደግ እየተሰራ መሆኑን አመልክተዋል።

አምባሳደር ምስጋኑ፣ ቱሪዝሙን በማስተዋወቅ፣ የውጭ ኢንቨስትመንት ከመሳብ አኳያ የቢዝነስና የኢንቨስትመንት ፎረሞችን በማዘጋጀት እንዲሁም አዳዲስ የገበያ ትስስሮችን በመፍጠር ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በትኩረት እየተሠራ እንደሆነ ጠቅሰዋል። ከዚህም የተነሳ የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲው ለኢትዮጵያ ልማት እና እድገት ድርሻው ጉልህ መሆኑን ተናግረዋል።

የቀድሞ ዲፕሎማትና የሰብዓዊ መብት ኮሚሽነር አምባሳደር ጥሩነህ ዜና በበኩላቸው እንደተናገሩት፤ ኢትዮጵያ በዲፕሎማሲው ረገድ ውጤት አስመዝግባለች። በተለይም ከፍተኛ እንቅስቃሴ ያደረገችበት ጊዜ ቢኖር ያለፈው ዓመት 2015 ዓ.ም ላይ ነው። ዓመቱ ኢትዮጵያ ትልቅ ስኬት ያስመዘገበች ነው የመባሉ ዋንኛው ምስጢር የብሪታንያ፣ ራሽያ፣ ሕንድ፣ ቻይና እና ደቡብ ኮሪያን ያቀፈው የብሪክስ አባል አገር እንድትሆን መደረጉ ሲሆን፣ ይህም ኢኮኖሚያዊ ዲፕሎማሲን የሚያሳይ ነው።

እርሳቸው እንዳሉት፤ ኢትዮጵያ የብሪክስ አባል መሆን መቻሏ በራሱ ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለም። ብዙዎች ስለብሪክስ ብዙ ግንዛቤ ላይኖራቸው ይችላል። ነገር ግን ኢትዮጵያ የዚህ ቡድን አባል አገር መሆኗ አንዱ የተፈላጊነቷ ብቻ ሳይሆን የተጽዕኖ ፈጣሪነቷም ጭምር ማሳያም ነው። ይህ ውጤት እንዴት መምጣት እንደቻለ ለሚያውቅ አካል ግን ጉዳዩ ትልቅ ስኬት የተገኘበት ነው። መጤን ያለበትም ከዚህ አኳያ ነው።

አምባሳደር ጥሩነህ፣ ኢትዮጵያ የብሪክስ አባል መሆኗ ትልቅ የዲፕሎማሲ ስኬት መሆኑን አጽንዖት ሰጥተው የተናገሩ ሲሆን፣ በኢኮኖሚያቸውም ከፍ ያሉ እና በፖለቲካው ዘርፍ የተሻሉ ናቸው የሚባሉ ከአፍሪካም ሆነ ከአህጉራችን ውጭ የሆኑ አገራት የብሪክስ አባል ለመሆን ጠይቀው እድሉን ማግኘት አልቻሉም። ኢትዮጵያ ከተመረጡ ጥቂት አገራት ውስጥ የምትገኝ ሲሆን፣ ይህ በብዙ ፈተና ውስጥ ሆና ያገኘችው ትልቅ ስኬት ነው ብለዋል።

የውጭ ኢንቨስትመንትን ለማሳደግ፣ የወጪ ንግዱን ለማሳለጥ እንዲሁም የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲኖር የነፃ ንግድ ቀጣናዎች በመቀላቀል በኢኮኖሚ ዲፕሎማሲው ሰፊ ሥራ መከናወኑን የሚናገሩት አምባሳደር ምስጋኑ፣ በኢኮኖሚ ዲፕሎማሲው በተሠሩ ሥራዎች ኢትዮጵያ በአፍሪካ ምርጥ የኢንቨስትመንት መዳረሻ ከሚባሉ ሀገራት ውስጥ ተካታለች ብለዋል። ኢትዮጵያ ከቀን ወደቀን ለምታመርተው ምርት የተለያየ የገበያ መዳረሻዎችን እያሰፋች ነው። በዚህ እንቅስቃሴዋም መልካም የሚባል ውጤት እያገኘች ነው።

ከአገራት ጋር ያለውን ትብብር የሚያጠናክሩ የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ እንቅስቃሴዎች መከናወናቸውን የሚያስረዱት አምባሳደሩ፣ በተለይ ተቋርጠው የነበሩ ግንኙነቶችን እንደገና በማስቀጠል እገዳ የተጣለባቸውን የፋይናንስ ድጋፍና የሰብዓዊ ርዳታዎች መጀመራቸውን አመልክተዋል። በየአገራቱ የሚከፈቱ የኢትዮጵያ ኤምባሲዎች የአገር ውስጥ ልማትንም ለማፋጠን የሚያግዙ እንዲሆኑ እየተደረገ ነው ብለዋል። የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲውን እንቅስቃሴ ለማስፋፋት ኢንቨስትመንት፣ የገበያ ዕድል፣ የቱሪዝም አቅምና የቴክኖሎጂ ሽግግር የሚገኙባቸው አካባቢዎችን ታሳቢ በማድረግ እንደሚሰራም ተናግረዋል።

አምባሳደር ጥሩነህ እንደሚናገሩት፤ ባለፉት ሁለት ሶስት ዓመታት የደረሰብን ፈተና ግልጽ ነው። እንደዚያ አይነቱ ችግር በሚያጋጥም ወቅት የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ መፍትሔ መስጠት የሚችል ነው። ለአብነትም ኢትዮጵያ የብሪክስ አባል አገር መሆኗ ሊያግዛት የሚችል ወዳጅ አገኘች ማለት ነው። ስለዚህ የሚያጋጥመን ተግዳሮት ካለ አብሮ የሚሆን አካል ከጎን መኖሩ ችግሩን አቅልሎ ለማየት ምቹ ከመሆኑም በላይ ለመጋፈጥ አቅም እንዲኖር የሚያደርግ ነው። ይህ ስብስብ በአሁኑ ጊዜ ባለው ሁኔታ የዓለም አቀፍ ኢኮኖሚ ከ30 እስከ 40 በመቶ የያዘ ነው። ይህን ቡድን መቀላቀል መቻል ትልቅ እድል ነው።

አምባሳደር ጥሩነህ፣ እኛ ኢትዮጵያውያን በኢኮኖሚያችን በጣም ማደግ እንሻለን። ይህ ጊዜ በጣም በከፍተኛ ደረጃ እየተነሳሳን ያለንበት ወቅት ነው። ስለሆነም የብሪክስ አባል መሆናችን ኢኮኖሚያችንን ለማሳደግ ለምናደርገው ሩጫ የሚጠቅመን ይሆናል ያሉት አምባሳደር ጥሩነህ፣ ለዚህ ደግሞ የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ ትልቅ ፋይዳ እንዳለው አመልክተዋል።

ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው፤ እንደ አገር ብሔራዊ ጥቅም ሊከበርባቸው የሚችሉ መድረኮችን በሙሉ በመከታተል ለጋራ ጥቅምና ዕድገት ይሰራል። ዲፕሎማሲ መነሻውም መድረሻውም የአገርን ሰላም፣ ልማትና ደኅንነት እንዲሁም ዕድገት ሊያረጋግጥ የሚችል መሆን አለበት። ኢትዮጵያ ወዳጅ ለመሆን ብቻ ወዳጅ የምትሆን አይደለም፤ ለአገር ሰላም እና ልማት ምን ይገኝበታል በሚል እሳቤ የሚደረግ ነው።

የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ሲቀረፅም በእነዚህ መርሆዎች ላይ ያተኮረ ነው። ከአገሮች ጋር በከንቱ ውዳሴ የሚደረግ ግንኙነት የለም። ለኢትዮጵያ ሰላም፣ ደኅንነት፣ ለአካባቢዋ፣ ከክፍለ አህጉሩም ሰላም አልፎ ለዓለም ሰላም የምትሰራበት ስለሆነ አሰላለፏ ከአይዲዮሎጂ ጋር ሳይሆን ከብሔራዊ ጥቅም ጋር ተያይዞ አንድ ቦታ የተቸከለ አይደለም። ስለዚህ ዛሬ ላይ ለልማታችን ተጨማሪ ፋይናንስ፣ የፖሊሲ ተመጋጋቢነት፣ አጋርነት እናገኛለን ብለን ነው በዋነኛነት በመሪ ደረጃ ተይዞ ብሪክስ እንድንቀላቀል የተደረገው ሲል መረጃው ያትታል።

በአሁኑ ጊዜ በዓለም አቀፍ ደረጃ በኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ ላይ የበለጠ ትኩረት የመስጠት አስፈላጊነት እውቅና አግኝቷል። ፖለቲካ ኢኮኖሚውን ሳይሆን፤ ኢኮኖሚው ፖለቲካን መምራት እንዳለበትም ይነገራል። የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ የመንግስት እና የመንግስት ግንኙነቶችን ለማካሄድ ኢኮኖሚያዊ መሳሪያዎችን በመጠቀም ኢኮኖሚያዊ ደህንነትን እና የሀገሪቱን ስትራቴጂካዊ ጥቅሞችን የማገልገል ጥበብ ሆኗል።

ይህ በመሆኑም ኢትዮጵያም ከዚህ የተለየ አካሔድ እንደሌላት ሚኒስትር ዴኤታው አምባሳደር ምስጋኑ ተናግረዋል። የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ ለኢትዮጵያ ልማት ዋነኛ የትኩረት አቅጣጫ ተደርጎ እየተሰራበት እንደሚገኝም አስረድተዋል። አሁን አሁን የፖለቲካ ዲፕሎማሲው የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲውን ማዕከል እንዲያደርግ የግድ ስለሚል በዚሁ መሰረት እየተሰራ እንደሆነም አመልክተዋል።

ሌላው የቀድሞ ዲፕሎማት አምባሳደር ጥሩነህ በበኩላቸው፤ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ፈጣን በሆነ መልኩ ማደግ ይጠበቅባታል። በአሁኑ ጊዜ በኢኮኖሚ እድገቱ ኢትዮጵያ እያንሰራራች እንደምትገኝም አመልክተው ለዚህ እድገት ደግሞ አገሪቱ የብሪክስ አባል መሆኗ ኢኮኖሚዋን ለማሳደግ ለምታደርገው ሩጫ ጠቃሚ ነው ብለዋል።

ማህበራዊ

# ሴቶች

# ከሰፊው የወላጅነት ባሕር የተቀዳው የልጅ አስተዳደግ

**አስመረት ብስራት**

የምኒሊክ ሁለተኛ ደረጃ መምህርት የነበረችው ወጣቷ ቆንጆ ከአንድ ሰው ጋር ተዋወቀች። ትውውቃቸው አድጎና ጎልብቶ ለቁም ነገር በቃ። እነዚህ አቶ ዘመኑ ሰናይና ወይዘሮ የሺ ወርቁ የተባሉ ጥንዶች በትዳር ተጣምረው በልጅ ሲባረኩ መጀመሪያ እቅፋቸው ውስጥ የገባችው የዛሬዋ የሴቶች አምድ እንግዳችን ወይዘሮ ሳራ ዘመኑ ናት።

ወይዘሮ ሳራ ዘመኑ ዛሬ ለሆነችው ሁሉ የወላጆቻ እጅ እንዳለበት ትመሰክራለች። ወላጅነትን ከወላጆቿ ተምራ በጥሩ የልጅ አስተዳደግ ሁለት ልጆቿን አሳድጋ ለቁም ነገር ያበቃችው ይች ሴት፤ ከሕይወት ልምዷና ከስራ ገጠመኞቿ የተቀዱ ማንም ማንበብና መፃፍ የሚችል ሰው አንብቦ ሊረዳው የሚችለው ጤናማ የልጆች አስተዳደግን የተመለከተ መፅሀፍ ፅፋ ለአንባቢዎች አቅርባለች።

እንግዳችን ወይዘሮ ሳራ ተወልዳ ያደገችው አዲስ አበባ ነው። የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቷን በናዝሬት ትምህርት ቤት። ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን በምስራቅ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማረች። አስራ ሁለተኛ ክፍልን ተፈትና ጉዞ ወደ አሜሪካ ሀገር ሆነ። አሜሪካን ሀገር የነርሲንግ የትምህርት ዘርፍ ተማራ የተዋጣላት ባለሙያ ሆነች።

ከ25 ዓመታት በፊት የነርስነት ትምህርቷን ጨርሳ ነበር ወደ ስራ የገባችው። በነርሲንግ የተለያዩ ሕክምና ተቋማት ላይ የሰራች ሲሆን አሁን ላይ በኮሚኒቲ ኮሌጅ ውስጥ ነርሲንግ ታስተምራለች። ቨርጂኒያ ኮሚኒቲ ኮሌጅ ውስጥ መምህርት፤ በሆስፒታል ሀኪም በመሆን የሀበሻ ኮሚኒቲ ውስጥ የተለያዩ ስራዎች ትሰራለች።

ባለትዳርና የሁለት ልጆቸ እናት የሆነችው ወይዘሮ ሳራ ዘመኑ ከሁለት አስርት ዓመታት በላይ ትዳር ውስጥ መቆየቷን ትናገራለች። በትዳሯ ስኬታማ ልጆቿንም በስርዓት አሳድጋ የመጀመሪያ ልጇ የሕክምና ትምህርት ቤት (ሜዲካል እስኩል) የሁለተኛ ዓመት ተማሪ ስትሆን ወንዱ ልጇም በዚህ ዓመት በሶፍትዌር ኢንጂነሪንግ ተመራቂ ተማሪ መሆኑን ትናገራለች።

እንደ ወይዘሮ ሳራ ገለፃ በውጭ ሀገር ሆኖ ልጅ ወልዶ ማሳደግ እጅግ ከባድ እንደሆነ ብዙዎች ያወራሉ። የትም ሀገር ቢሆን ማሕበረሰብ የራሱ የሆነ ስርዓትና ስነ ምግባር አለው። ይህ ማለት ሰው የሀገሩን ማንነት ሳይለቅ ራሱን ሆኖ በስርዓት ማሳደግ ሲሞክር ምንም አይነት ማስመሰል ስለማይቻል ልጆች በራሳቸው የሚተማመኑ የባሕል ግጭት የማይኖርባቸው ልጆች ይሆናሉ።

ወላጅነት ራስን መሆን ነው። ከባሕል ከወግ ከትናንት ማንነት ከራስ አስተዳደግም ጭምር በተቀመረ ልምድ ግብረ ገብንና ስርዓትን ማሳወቅ ልጆችን አታድርጉ የሚባሉትን ነገር በምክንያት ማስረዳት ተገቢ መሆኑን ነው ወይዘሮ ሳራ የምትናገረው።

እንደ ወይዘሮ ሳራ በራሱ የሚተማመን ልጅ ለማሳደግ ሁልጊዜ የምናደርገው ነገር አንድ አይነት የማይቀያየር መሆን አለበት። ይህም ማለት ሕግ ካወጣን ሁልጊዜ በዚያ ሕግ መመራት አለብን፤ አይሆንም ብለን የወሰነውን ነገር አይሆንም ነው። በተቻለ መጠን እናት እና አባት አንድ አይነት አቋም መያዝ አለባቸው። እናም ለልጆቻችን (consistency) ተከታታይነት ያለው አካሄድ መጠቀም በጣም አስፈላጊ ነው። እነሱም የሚፈልጉት ይህንኑ ነው።

ቤታችን ውስጥ ሕግ ያስፈልገናል። ልጆቹ የሚመሩበት በእኛ የወጣ እና ልጆቹ የሚከተሉት ሕግ። ይኼ በጣም አስፈላጊ ነው፤ ይኼ ለልጆች ውስጣዊ ደህንነት ይሰጣቸዋል። ራሳቸውን መምራት ስለማይችሉ ሕግ በእርግጥም ያስፈልጋቸዋል። ያ ሕግ ዛሬ የሚሰራ ነገ የሚሻር መሆን የለበትም፤ ልጆቹን ግራ ያገባቸዋል። ይህ በራስ መተማመናቸው ላይ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው። ታዲያ በዚህ ሕግ ላይ የተመሰረተ ጥሩ ግንኙነት ያስፈልገናል፤ ሕጉን ማከብራቸውን መከታተል ያስፈልጋል። ከእኛ ፍቃድ ውጪ ያንን ሕግ መሻር እንደማይቻል ማወቅ አለባቸው ትለናለች።

ስለእነሱ፤ ስለማንነታቸው ስንናገር አዎንታዊ (postive) መሆን አለበት። ይህ ታዲያ ከውልደታቸው ከዳይፐር ቅያሬ ሰዓት ይጀመራል፤ የምንላቸውን ይሆናሉ፤ የምንላቸውን ነገር ልባቸው ውስጥ ይፅፋሉ፤ ያትማሉ፤ ምክንያቱም እኛ ነን ቅርባቸው። ከማንም በላይ የሚያምኑት የሚወዱት እኛን ነው። ለእራሳቸዉ ያላቸው አመለካከት፣ ራሳቸውን የሚያዩበትን መነፅር ጥሩ እንዲሆን፤ የምንመራቸውን ነገር አስበን በጣም ጥንቃቄ ማድረግ አለብን። ለራሳቸው ያላቸው አመለካከት በራስ መተማመናቸው እንዲጎለብት መሰረት ነው። ሌላም የውጪ ሰው አሉታዊ ነገር እንዲላቸው መፍቀድ የለብንም። አንድ ሰው የተናገረውን ዉስጣቸው ይዘው ራሳቸውን በዚያ መነፅር ሊያዩ ይችላሉ። ስለዚህ ጥንቃቄ ማድረግ አለብን።

ልጆች ትችት ማለት ምን ማለት እንደሆነ አያውቁም፤ ለትችት አልደረሱም። ልጆችን ከተቸናቸው ያን ትችት ወይም ተቃርኖ በመፍራት መስራት የሚፈልጉትን ወይም መስራት ያለባቸውን አይሰሩም። ይልቁንስ መምራት፤ ትክክል የሆነውን እና ያልሆነውን ማስተማር፤ ማበረታታት፤ ትጋታቸውን ማድነቅ በጣም አስፈላጊ ነው። ይህ ለልጆች በራስ መተማመን ወሳኝ ነው። ለዚህ ደግሞ ትልቁ ሀይል የወላጅ ነዉ። ልጆች እራሳቸውን የሚያዩበትን መነፅር መሰረቱን መጣል እና መቅረፅ ያስፈልጋል።

ይህም በተመሳሳይ መልኩ ከልጅነት መጀመር አለበት። በተለይ በልጅነት እድሜያቸው ሁሉንም እንፈልጋለን ለሚሉ ልጆች ሁለት ወይም ሶስት ነገር መርጦ የቱን ትፈልጋለህ (ትፈልጊያለሽ) ብሎ ማስመረጥ፤ ልብስ መግዛት ሊሆን ይችላል፤ ማድረግ የሚፈልጉት ነገር ሊሆን ይችላል፤ የቤት ውስጥ ስራ ማገዝ ሊሆን ይችላል፤ በሁሉም ሁኔታ ከማዘዝ ይልቅ ምርጫ እንዲኖራቸው ማስተማር፤ ይህ "እራሴ መምረጥ እችላለሁ" የሚል ስሜት ያጎለብትላቸዋል፤ በራስ መተማመናቸው ላይ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋል በማለት ታብራራለች።

"በእኛ ቤት የተለያዩ አይነት የልጅ አስተዳደጎችን ተከትለናል። ሁለታችን የተማርን ነን። ተሰደን መሄዳችንን ባንረሳውም የመጣንበት ሀገር ባሕል ማንነት ነግረን ሳይሆን ኖረን አሳይተናቸዋል። ከሄድንበት ሀገር ሰው አስተሳሰብ ጋር አስታርቀን እየኖርን ልጆችን ማሳደግ ችለናል። የኛ ባሕል የሚያሳፍር ያልሆነ የሚደብቅ ሳይሆን ተኮርቶበት አደባባይ የሚወጣ መሆኑን ነው ነግረን ያሳደግናቸው።"

ልጆቻችንን ሁሌ መመረቅ አንረሳም። አንደበታችን ምርቃት ብቻ ይሁን። ከአፋችን አትረባም አንተስ አንቺስ እያልን የምንረግመው ከኛ ይራቅ። ቃል ኃይል አለው። ልጆች ከልጅነታቸው ለሌሎች ሰዎች እንዴት ክብርና ትህትና ማሳየት እንዳለባቸው የሚያሳይ ጥሩ ልምምድ ነው። ስለዚህ እኛ ልጆቻችንን በምርቃት ነው ያሳደግነው ምርቃቱም ሰርቷል ትላለች።

ልጆች የሰጠናቸውን የሰሙትን እጥፍ አድርገው መልሰው ይሰጡናል። ስለዚህ እንዲመልሱልን የምንፈልገውን ብቻ እንስጣቸው። ያ ማለት በመልካም ስነምግባር ለማስተማር ከፈለግን መልካም እሴቶችን እየነገርንም እየኖርንም እናሳያቸው ብላለች።

በሕይወት ልምዷም ሆነ ከወላጆቿ ያገኘችውን የልጅ አስተዳደግ ሁሉም ይማርበት ዘንድ "ጤናማ የልጆች አስተዳደግ" የሚል ልጆችን እንደየ እድሜያቸው በአግባቡ በጥበብ ማሳደግ የሚል ሀሳብን የያዘ መፅሃፍ አበርክታለች። ልጆች ከተወለዱ ጊዜ ጀምሮ ወላጆች የሚያደርጉት ነገር ነው መጨረሻ ላይ ሰው ሲሆኑ የሚመራቸው የሚል ሀሳብ ያላት ወይዘሮ ሳራ ሰው ሁሉ የልጅነት ስርዓት ውጤት በመሆኑ ነገን ብሩህ ለማድረግ ትውልድ ላይ መስራት አማራጭ የማይኖረው መሆኑን ታስረዳለች።

ዓለምን ውብ አድርጎ ለመስራት በልጆቹ በኩል መሄድ ይገባል የምትለው ወይዘሮ ሳራ፤ ለልጆች የምትመች ዓለምን ለመፍጠር የራሴን ኃላፊነት መወጣት የሁሉም ማሕበረሰብ ድርሻ ነው በማለት ትገልጻለች። ህጻናት ከኛ አብራክ የወጡ እና ተመሳሳይ የሆኑ ቢመስለንም፣ ወላጆችም በአንድ አይነት የአስተዳደግ ዘዴ ለማሳደግ ብንሞክርም ልጆች የተለያየ ማንነትን ያዩ ናቸው የምትለው ሳራ፤ ልጆች ላይ የምናስተውለውን ልዩነት ሳንሰብራቸው ደግፈን እና አጎልብተን ጥሩ ዜጋ እንዲሆኑ ማድረግ ይገባናል ትላለች።

ብዙውን ጊዜ በኢትዮጵያውያን ዘንድ ልጆች ትምህርት ተምረው እኛ በምንፈልገው መስክ ብቻ እንዲያድጉ ነው የምናደርጋቸው። ነገር ግን ልጆች ስሌላው የሕይወት ክፍል ሳያውቁ ያድጋሉ ያ ደግሞ ልጆች አድገው ከሕይወት ጋር በሚኖራቸው ግብግብ የስነልቦና ቀውስ ይፈጠርባቸዋል። ልጆቻችን ስናሳድግ አንዳንዴ እድሜያቸው የሚደርሱበት ኃላፊነት ምን ማለት እንደሆነ እንዴት እንደሚወጡት እየነገርናቸው ማሳደግ ይገባናል ትላለች። ልጆቻችን በሚሰማሩበት ቦታ ሁሉ እኩል አስተዋጽኦ እንዳላቸውም መንገር ያስፈልጋል። ሁላችንም ዓለም ያለን ሰዎች የራሳችን ተሰጥኦና ዝንባሌ አለን። በመሆኑም ልጆች ያላቸውን ተሰጥኦ እንዲያጎለብቱት በማድረግ በማንነታቸው ደስተኛ ሆነው እንዲኖሩ ማድረግ የወላጆች ኃላፊነት ነው።

ሁሉም ሰው በእኩል የኑሮ ደረጃ ላይ ባይኖርም፤ አንድ አይነት አስተሳሰብ ባያራምድም ልጁ መጥፎ እንዲሆንበት የሚፈልግ የለምና ወላጅነትን በጥበብ በማድረግ፤ የተፃፉ ልምዶችን በማንበብ፤ የተለያዩ ውይይቶችን በማድረግ ነገ ሀገርን እንደሀገር ለማስቀጠል የሚበቁ ብቁ ዜጎች ለማፍራት የእያንዳንዳችን ድርሻ የላቀ መሆኑን ልንገነዘብ ይገባናል ትላለች።

በመጨረሻም ሕፃናት አይምሮ ብሩህ እና ፈጣን እንዲሆን ከምንመግባቸው ምግብ ባልተናነሰ መልኩ ሌሎች ማነቃቅያዎችን እና እንክብካቤዎችን ይፈልጋል ትለናለች። ሁሉም ሕፃናት ሲወለዱ ጂኒየስ የመሆን ብቃት ይዘው ነው የሚወለዱት። ሆኖም እያንዳንዱ የጭንቅላት ህዋስ ባለው ብቃት (potential) ልክ ካልተነቃቃ በልጁ አይምሮ ውስጥ ያሉት የነርቭ ግንኙነቶች (synapse) እየተወገዱ ወይም እየደከሙ ይሄዳሉ።

እነዚህ የነርቭ ግንኙነቶች (synapse) በጊዜ ከተነቃቁ ግን እያደጉ እየበለፀጉ ይሄዳሉ። በዚህም ሕፃኑ ባለ ብሩህ አይምሮ ባለቤት ይሆናል። በጣም የሚገርመው የልጆች አይምሮ አንድ አዋቂ ከሚያስበው እና ከሚያመላልሰው ሃሳብ በላይ ማስተናገድ እና ማከናወን ይችላል።

ለምሳሌ አዋቂ ከሆነ በኋላ የተለያዩ ቋንቋዎች መልመድ በጣም ይከብደናል ሕፃናት ግን በተወሰነ ጊዜ ውስጥ መልመድ መስማት ብሎም መናገር ይችላሉ። ስለዚህ ይሄንን ብሩህ አይምሮ ደሞ ማነቃቃት፣ መቅረፅ፣ ማዘጋጀት እና መስመር ማስያዝ የወላጆች እና የአሳዳጊዎች ኃላፊነት ነው።

ወላጆች አንድ ማስተዋል ያለባችሁ ነገር ልጆቻችሁ ሁሉ ሳይንቲስት ፓይለት ዶክተር ወይም ኢንጅነር መሆን አይጠበቅባቸውም። ምርጥ አርቲስት ምርጥ ሰዓሊ ወይም ምርጥ ባለሙያ መሆን በራሱ ትልቅ ስኬት ነው። በመሆኑመ ልጆቻችሁን ከሌሎች ልጆች ጋር ማነፃፀር የለባችሁም ከዛ ይልቅ የራሳቸውን ታለንት ወይም ተሰጦ እንዲከተሉ እና መንገድ እንዳይስቱ ብቻ መርዳት ያስፈልጋል ትላለች። ከወይዘሮ ሳራ በአብዛኛው ምክርና ትምህርትን ያዘለ ውይይታችንን በዚህ መልኩ አብቅተናል።



ወ/ሮ ሳራ ዘመኑ ሰናይ

**ወላጅነት ራስን መሆን ነው። ከባሕል ከወግ ከትናንት ማንነት ከራስ አስተዳደግም ጭምር በተቀመረ ልምድ ግብረ ገብንና ስርዓትን ማሳወቅ ልጆችን አታድርጉ የሚባሉትን ነገር በምክንያት ማስረዳት ተገቢ ነው**

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

**ሙሉጌታ ብርሃኑ**

አዲስ ዘመን ትናንት እንዴትስ አለፈ፤ ትናንትን በዛሬ በአዲስ ዘመን ድሮ ትውስታዎች የአጭር ቀሚስ ቁጥጥር፤ የ40 ዓመቷ ሴት፤ 22 ጠንቋዮች የሳምንቱ አጋጣሚና ሌሎች ጉዳዮችም ተካትተዋል።

### የአጭር ቀሚስ ቁጥጥር በሐረር

ሐረር፡- (ኢ-ዜ-አ-) በሐረር ከተማ ውስጥ አጫጭር ቀሚስ እየለበሱ በሚዘዋወሩት ሴቶች ላይ ጥብቅ ቁጥጥር እየተደረገ መሆኑን የሐረር አውራጃ ፖሊስ አዛዥ ሌተናል ኮሎኔል ኃይለሚካኤል ገብሬ ገለጡ፡፡

በተደረገው ቁጥጥር መሠረት በሐረር ከተማ ውስጥ የሀገርን ባህል የሚያጎድፍ ልብስ ለብሰው የተገኙት 67 ልጃገረዶችና ሴቶች 2ኛ ፖሊስ ጣቢያ እየቀረቡ ዳግመኛ ላለመልበስ መፈረማቸውን ሌተናል ኮሎኔል ኃይለ ሚካኤል አስረድተዋል፡፡ ይኸው አፈጻጸም ለወደፊቱ በየጣቢያው ተላልፎ በሚገባ በሥራ ላይ እንደሚውል ታውቋል፡፡

በዚሁ ይዞታ በከተማው ውስጥ ይታይ የነበረው የአጭር ቀሚስ ለባሾች ቁጥር መቀነሱንና ለወደፊት ጨርሶ እንደሚጠፋ ሌተናል ኮሎኔል ኃይለሚካኤል ገብሬ እምነታቸው መሆኑን ገልጠዋል፡፡

**(አዲስ ዘመን፣ ጥቅምት 2 ቀን 1962 ዓ.ም)**

### የ40 ዓመት ሴት በአንድ ጊዜ ሦስት ልጆች ወለዱ

ሐረር፡-(ኢ.ዜ.አ) ወይዘሮ ፋጡማ ኢብሮ የተባሉ የ40 ዓመት ሴት ሐረር ከተማ በሚገኘው፣ በምሥራቅ አርበኞች ሆስፒታል ውስጥ ባለፈው ዓርብ 3 ሕጻናትን በአንድ ጊዜ መገላገላቸውን የሆስፒታሉ አስተዳደር አቶ ሽፈራው አቢቢ አስታወቁ።

ከሕጻናቱም መካከል መጀመሪያ የተወለደው ወንድ 4 ኪሎ ከሃያ አምስት ግራም ክብደት ሲኖረው፣ ተከትለው የተወለዱት ሌሎች አንድ ወንድና ሴት ደግሞ እያንዳንዳቸው አንድ ኪሎ ከ20 ግራም ክብደት እንዳላቸው ተገልጧል።

**(አዲስ ዘመን፣ ግንቦት 7 ቀን 1971 ዓ.ም)**

### 22 ጠንቋዮች ራሳቸውን አጋለጡ

ደሴ፡- (ኢ.ዜ.አ) ወሎ ውስጥ፣ በደላንታ ወረዳ የኢላና ትምህርት ቤት መምህራን ከጣርዳት፣ ከደሀናንና ከዝባን የገበሬ ማኅበራት ጋር በመተባበር በመካከላቸው የተሰገሰጉትን 22 አባይ ጠንቋዮች ራሳቸውን አጋልጠው ክቡር ወደ ሆነው የሥራ መስክ እንዲሰማሩ አደረጉ።

እነዚሁ 22 አባይ ጠንቋዮች በተሰጣቸው ትምህርት አምነው ድቤዎችን (ከበሮዎችን)፣ እንዲሁም በእጃቸው ይገኙ የነበሩትን ልዩ ልዩ የጥንቆላ ዕቃዎችንና መጻሕፍት ለገበሬ ማኅበራቱ በራሳቸው ፈቃድ አስረክበዋል። አባይ ጠንቋዮቹ ካስረከቧቸው ዕቃዎች ውስጥ፣ በተለይ ከበሮዎቹ በአካባቢው ለሚቋቋመው የኪነት ቡድን መገልገያ እንዲሆን መሰጠቱ ተገልጧል።

**አዲስ ዘመን መጋቢት 23 1971ዓ.ም**

### በከበርቴው ይቀለብ የነበረው ዘንዶ በገበሬው ተገደለ

በኢሉባቦር ክፍለ ሀገር፣ ዱጳ በተባለው ቀበሌ አንድ የቀድሞው የመሬት ከበርቴ ከአንድ ገበሬ ላይ እየወሰደ ይቀልበው የነበረ አንድ ዘንዶ ሰሞኑን በገበሬው ተገደለ፡፡

ነጋሽ ተመመ የተባለው የቀድሞው የመሬት ከበርቴ ከገበሬው በግ እየነጠቀ ቆሎ ተብሎ በተሰየመ እንጨት ሥር እያደረ ዘንዶውን ይቀልብ የነበረ መሆኑን ተገልጧል፡፡

ዘንዶው ሰሞኑን ነጋሽ ተመመ በሌለበት እንደልማዱ ወደ እንጨቱ ሲመጣ በአካባቢው የተሠማሩትን፣ የገበሬውን ከብቶች በማግኘቱ ከመካከለቻው አንዷን በግ ሲይዛት ደርሶ ገበሬው በጦርና በመጥረቢያ ጨፍጭፎ ገድሎታል፡፡

ዘንዶው ቁመቱ ስምንት ሜትር፣ ጎኑ 60 ሳንቲ ሜትር ሲሆን፤ በአሁኑ ጊዜ ቆዳው በኤግዚቢትነት በአካባቢው የገበሬ ማኅበር ጽ/ቤት የሚገኝ መሆኑን የዳሪሙ ወረዳ ፖሊስ አዛዥ ገልጸዋል፡፡

**አዲስ ዘመን፣ ጥቅምት 23 ቀን 1979ዓ.ም**

### ተቆጣጣሪ በመምሰል ያጭበረበረው ተቀጣ

ደሴ፡- (ኢዜአ) በደሴ ከተማ ውስጥ ምንም አይነት ሥልጣን ሳይኖረው የአሥር አለቃ ነኝ በማለት ከገጠር ወደ ከተማ የሚገባውንና የሚወጣውን እህል፣ ስኳርና ልዩ ልዩ ሸቀጣ ሸቀጦች በመፈተሽ ሲያወናብድ የተገኘው ዓሊ መሐመድ በ3 ወር እስራት እንዲቀጣ የ04-01-01 ቀበሌ ማኅበር የፍርድ ሸንጎ ከትናንት በስቲያ ወስኖበታል።

በተከሳሹ ላይ የእስራት ቅጣት ሊወሰንበት የቻለው ባልተሰጠው ሥልጣን በመንገድ ላይ እየጠበቀ ስኳርና ሸቀጥ ጭነው ወደ ገጠር የሚወጡትንና እህል ጭነው ወደ ከተማ የሚገቡትን መኪናዎች እያስቆመ በመፈተሽ የተመቸውን ጥቅም በመቀበል ሲለቅ ያልተመቸውን ደግሞ ወደ 3ኛ ፖሊስ ጣቢያ በማቅረብ አወናብዶ ለማስቀጣት ሞክሮ እንደነበር በማረጋገጡ ነው፡፡

**( አዲስ ዘመን፣ የካቲት 19 ቀን 1969ዓ.ም)**

### ፖሲስ ጣቢያ

ግንቦት 14 ቀን ከጠዋት 2 ሰዓት ከ20 ደቂቃ ሲሆን ሰፈሩ ቄራ ሰፈር የሆነ ገብረጻድቅ ተስፋዬ የሚባል ሰው ያንድ እግር ጫማ፣ 2 የቆዳ ገንባሌ ይዞ ሲሔድ በእቴጌ መነን መንገድ ተገኝቶ በጥርጣሬ ኪዳኔ ይማም በሚባል ፖሊስ ተይዞ መጥቶ ዋቢውን እስኪያቀርብ ታስሯል፡፡

**(አዲስ ዘመን፣ ሰኔ 5 ቀን 1936 ዓ.ም)**

ግንቦት 14 ቀን ከቀኑ 4 ሰዓት ሲሆን የሰሜን ምሽግ ገፈርሣ የሚጠብቁት የጦር ሚኒስቴር ወታደሮች ኃይለማሪያም ዘለቀና ማሞ ወልደጻድቅ የሚባሉት ሌቦች ሌሊት ሁለት ሆነው 7 ሰዓት ላይ የምሽጉን ቆርቆሮ ሰርቀው ሲሔዱ ሮምታ ብንተኩስ ተሁለቱ አንዱን ሌባ ገደልነው ሲሉ አመልክተዋል፡፡

(አዲስ ዘመን፣ ሰኔ 5 ቀን 1936 ዓ.ም)

### የሳምንቱ አጋጣሚ

እሁድ እለት አምባሳደር ቡና ቤት ቁጭ ብለን ሻይ ስንጠጣ አንድ የምናውቀው ሰው በመጠጥ ኃይል ተሸንፎ መዝጊያውን የከፈተ መስሎት ከመስተዋት ጋር ሲታገል በማየታችን በጣም አስቆናል፡፡

**ሺመክት አስሙ**

**አዲስ ከተማ**

...............

አንድ መጽሔትና ጋዜጣ ሻጭ ልጅ ለአንድ የውጭ ዜጋ ታይም መጽሔት ለመሸጥ በሚያሳየው ጊዜ የውጭ ሰው ሐውማች ብሎ ሲጠይቀው ልጁ ጣቱን እያሳየ ዋን ብር ዋን ስሙኒ ብሎ መለሰለት፡፡

**(አዲስ ዘመን፣ ታህሳስ 2 ቀን 1968 ዓ.ም)**

# ዓለም አቀፍ



## በታንዛኒያ በደረሰ የመሬት መንሸራተት የ22 ሰዎች ሕይወት አለፈ

በሰሜናዊ ታንዛኒያ በሚገኝ ሕጋዊ ባልሆነ የማዕድን ማውጫ ላይ በደረሰ የመሬት መንሸራተት አደጋ 22 ሰዎች መሞታቸው ተገለጸ። አደጋው የደረሰው ቅዳሜ ዕለት በባሪዲ ወረዳ ሲሚዩ ክልል ንጋሊታ ማዕድን ማውጫ ነው ሲሉ የወረዳው ኮሚሽነር ሲሞን ሲማለንጋ ተናግረዋል።

በከባድ ዝናብ ምክንያት ሥራ እንዲቋረጥ በተገደበት አካባቢ የተወሰኑ ሰዎች የማዕድን ማውጣት ከጀመሩ በኋላ አደጋው መድረሱን ለሮይተርስ የዜና ወኪል ተናግረዋል። ፕሬዚዳንት ሳሚያ ሱሉሁ ሃሰን በዜናው “ታላቅ ኀዘን” እንደተሰማቸው ገልጸዋል።

“እነዚህ ታንዛኒያውያን ድሃ ማዕድን አውጪዎች ሲሆኑ ለራሳቸው እና ለቤተሰቦቻቸው መተዳደሪያ ለማግኘት ይጥሩ የነበሩ ናቸው” ሲሉ ኤክስ ላይ ጽፈዋል። በማዕድን ማውጫው ውስጥ ከ19 እስከ 20 ሰዎች አደጋ እንደደረሰባቸው መስማታቸውን ነገር ግን 22 አስከሬኖች መውጣቱን ሲማሌንጋ ተናግረዋል።

የአካባቢው የእሳትና የነፍስ አድን ተጠባባቂ አዛዥ ፋውስቲን ማቲቱ “ከእንግዲህ ወዲህ በፍርስራሹ ውስጥ የተቀበሩ አስከሬኖች ስለሌሉ” ፍለጋው ተጠናቋል ማለታቸውን አጃንስ ፍራንስ ፕሬስ የተባለው የዜና ወኪል ዘግቧል። ሲማሌንጋ እንደገለጹት ቡድኑ በማዕድን በበለጸገው አካባቢ ከሦስት ሳምንታት በፊት ማዕድን ማውጣት የጀመረ ሲሆን ይህም መንግሥት የደህንነት ሂደቶችን ከማምጣቱ በፊት ነው።

በአካባቢው እየጣለ ያለው ከባድ ዝናብ ጎርፍ በማስከተሉ ምክንያት በአካባቢው ማዕድን ማውጣት ተከልክሏል። “የክልሉ ማዕድን ሠራተኛ ጎብኝቷቸው የማዕድን ቁፋሮውን አስቆሟቸዋል” ብለዋል ሲማለንጋ።

በዓለም ትልቅ ከሆኑት የወርቅ አምራቾች አንዷ በሆነችው ታንዛኒያ ቁጥጥር ያልተደረገበት እና በሕገ-ወጥ መንገድ ማዕድን ማውጣት የተለመደ ነው ሲል ቢቢሲ ዘግቧል።

## አሜሪካ አዲሱን የታይዋን መሪ ‘እንኳን ደስ አልዎ’ ማለቷ‘ትልቅ ስህተት ነው’ ስትል ቻይና ወቀሰች



ከቅዳሜው የታይዋን ምርጫ ውጤት በኋላ ዩናይትድ ስቴትስ ለሀገሪቱ ነፃነት ለሚታገሉ ሰዎች “በጣም የተሳሳተ መልዕክት” አስተላልፋለች ስትል ቻይና ወቀሰች። የአሜሪካው ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አንቶኒ ብሊንከን ውጤቱን ተከትሎ ለተመራጩ የታይዋን ፕሬዚዳንት ዊልያም ላይ የእንኳን ደስ አልዎት መልዕክት ልከዋል።

መልዕክቱን ዋሸንግተን ከታይዋን ጋር ያላትን ግንኙነት ይፋዊ ባልሆነ መንገድ ብቻ ለማስቀጠል ያላትን ቁርጠኝነት የሚጥስ ነው በማለት ቤይጂንግ ገልጻለች። ተመራጩ ፕሬዚዳንት ላይ ታይዋንን ከጊዜ ወደ ጊዜ “ጨቋኝ እየሆነች ከመጣችው ቻይና” ለመጠበቅ ቃል ገብተዋል።

ታይዋንን እንደ ግዛቷ የምትመለከታት ቻይና፣ ከዚህ የተለየ ሃሳብ ያለውን ማንኛውንም መንግሥት አጥብቃ ትቃወማለች። በታይፔ እና በዋሸንግተን መካከል ያለውን አጋርነት አፅንኦት የሰጡትን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ብሊንከንን ጨምሮ ከምርጫው በኋላ ለአዲሱ ታይዋን ፕሬዚዳንት በርካታ ሀገራት የእንኳን ደስ አልዎ መልዕክቶችን አስተላልፈዋል።

“የጋራ ጥቅማችንን እና እሴቶቻችንን ለማስቀጠል ከዶክተር ላይ እና ከታይዋን መሪዎች ጋር ለመሥራት እንጠባበቃለን” ሲሉ በመግለጫቸው ተናግረዋል። ብሊንከን አክለውም ከታይዋን ታላላቅ አጋሮች አንዷ የሆነችው አሜሪካ በአካባቢው “ሠላም እና መረጋጋት ለማስጠበቅ ቁርጠኛ መሆኗን” አፅንኦት ሰጥተዋል። የዩናይትድ ስቴትሱ ከፍተኛ ዲፕሎማት አክለውም እንዲህ ዓይነቱ ትብብር “የእኛን የቆየ ይፋዊ ያልሆነ ግንኙነታችንን የሚያጠናክር እና ከአሜሪካ የአንድ ቻይና ፖሊሲ ጋር የሚጣጣም መሆን አለበት” ብለዋል።

በፖሊሲው መሠረት ዩናይትድ ስቴትስ ከታይዋን ደሴት ይልቅ ከቻይና ጋር መደበኛ ግንኙነት እንዳላት ነው። ቤይጂንግ በበኩሏ ታይዋንን የምትመለከተው አንድ ቀን እንደምትዋሃዳት የተገነጠለች ግዛቷ ነው። የብሊንከን መልዕክት ከቤይጂንግ የሰላ ትችት አስተናግዷል። ለታይዋን የሚሰጥን ማንኛውንም የድጋፍ መግለጫ ሀገሪቱን ወደ ነፃ እና ሉዓላዊ ሀገርነት ለመቀየር ተስፋ ላለው ዕጩ እና የፖለቲካ ፓርቲ ሕጋዊነትን እንደመስጠት ትቆጥረዋለች።

የቻይና የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ባወጣው መግለጫም፣ የብሊንከን እንኳን ደስ አልዎት መልዕክት ዋሸንግተን ከታይዋን ጋር “በባህል፣ በንግድ እና በሌሎች ይፋዊ ባልሆኑ ግንኙነቶችን ብቻ” እንደሚወሰን የገባችውን ቃል የሚጻረር ነው። የታይዋን ጥያቄ “በቻይና እና በአሜሪካ ግንኙነት ውስጥ መታለፍ የሌለበት የመጀመሪያው ቀይ መስመር” መሆኑን አፅንኦት ሰጥቶ ዲፕሎማሲያዊ ቅሬታ መቅረቡንም ገልጿል።

“ዩናይትድ ስቴትስ ከታይዋን ጋር ያላትን ማንኛውንም ዓይነት ይፋዊ ግንኙነት እና በታይዋን ጉዳዮች በማንኛውም መንገድ ወይም በማናቸውም ምክንያት ጣልቃ መግባቷን ቻይና አጥብቃ ትቃወማለች።” የቤይጂንግ መግለጫ ታይዋን አዲሱን መሪ ከመረጠች ከጥቂት ሰዓታት በኋላ የቀድሞ የአሜሪካ ባለሥልጣናትን ያቀፈ ልዑክ በታይዋን ውስጥ ካሉ ታዋቂ የፖለቲካ ሰዎች ጋር እንዲወያይ ይፋዊ ባልሆነ መንገድ ለላከችው ዋሸንግተን ማስጠንቀቂያ ሊሆን ይችላል ተብሏል።

የምርጫውን ውጤት በተቀበሉት የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን የተሠማራው የልዑካን ቡድኑ የቀድሞውን የአሜሪካ ብሔራዊ ደኅንነት አማካሪ እና የቀድሞ ምክትል የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አካቷል። ዩናይትድ ኪንግደም፣ ፈረንሳይ እና ጀርመንን ጨምሮ ሌሎች ምዕራባውያን ሀገራት ለአዲሱ መሪ የእንኳን ደስ አልዎ መልዕክት አስተላልፈዋል ሲል ቢቢሲ ዘግቧል።

# ነፃ ሃሳብ



ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፣ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

**በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)**

fenote1971@gmail.com

# ወደ አዲስ ምዕራፍ የሚያሸጋግር ምክረ ሃሳብ

እንደ ሀገር ከገባንበት ቀውስ መውጫና መዳኛ ብቸኛ መንገዳችን ሀቀኛና ገለልተኛ ሀገራዊ እርቅና የሽግግር ፍትሕ ነው። የሽግግር ፍትሕ የባለሙያዎች ቡድን ላለፉት ስምንት ወራት ካዘጋጇቸው መድረኮች ያሰባሰቡትን ሀሳብ በመቀመር በዚያ ሰሞን ምክረ ሀሳብ ሰጥተዋል። ይህ ምክረ ሀሳብ በአግባቡ ስራ ላይ ከዋለ ለሽግግር ፍትሁ ትልቅ ግብዓት እንደሚሆን ይታመናል። በሽግግር ፍትሕ የሚታዩ ጉዳዮችን የሚዳኝ ልዩ ፍርድ ቤት በማቋቋም ክስ የመስማትና ውሳኔ የመስጠት ተግባር ማከናወን የሚችል አማራጭ ምክረ ሐሳብ፣ ከሕዝባዊ ምክክር ተሳታፊዎችና ከሽግግር ፍትሕ የባለሙያዎች ቡድን ይጠበቃል ።

የሽግግር ፍትሕ የባለሙያዎች ቡድን የቅድመ ረቂቅ ፖሊሲ ሕዝባዊ ምክክርና የግብዓት ማሰባሰብ ሥራዎችን ከየካቲት 27 ቀን 2015 ዓ.ም. እስከ መስከረም 30 ቀን 2016 ዓ.ም፣ ሁሉንም ክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች በማሳተፍ ሲያከናውን መቆየቱን፤ አሥራ ሦስት አባላት ያሉት የባለሙያዎች ቡድን ባዘጋጃቸው 58 መድረኮች 3391 ሰዎች በምክክር የተሳተፉ መሆኑን፣ ከእነዚህ ውስጥ 1,388 ተሳታፊዎች ተጎጂዎች መሆናቸውን ቡድኑ ይፋ ማድረጉ ይታወሳል።

በሕዝባዊ ምክክሩ ውይይቱ በየትኞቹ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ የክስ ሒደት ሊኖር እንደሚገባ ከቀረቡ አማራጭ ሐሳቦች መካካል፣ ከአብዛኞቹ ተሳታፊዎች ጉልህ በሆኑ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ወይም ወንጀሎቹ ላይ ያተኮረ የክስ ሒደት ሊኖር እንደሚገባ መናገራቸው ተገልጿል። በሌላ በኩል ቁጥራቸው ቀላል የማይባሉ ተሳታፊዎች የክስ ሒደቱ ሁሉንም የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ወይም ወንጀሎች ያካተተ መሆን እንዳለበት አመላክተዋል።

የወንጀል ምርመራና ክስ የመመሥረት ሒደት አማራጭ ሐሳብ ላይ አብዛኞቹ አሁን ካለው የምርመራና የዓቃቤ ሕግ ተቋም ውጪ የምርመራና የክስ ሒደቶችን የሚያስተባብር፣ ልዩ ነፃና ገለልተኛ የምርመራና የክስ ሥራ የሚያከናውን ተቋም በማቋቋም፣ እንዲሁም የተሻለ ዕውቀትና ልምድ ያላቸውን የምርመራ ባለሙያዎችንና ዓቃቢያን ሕግ በመመደብ ሥራው መከናወን እንዳለበት ጠቁመዋል።

እውነታን የማፈላለግና ዕርቅን የሚመለከቱ ተግባራት በየትኛው ተቋም ይከናወኑ በሚል በቀረበው አማራጭ የፖሊሲ ሐሳብ አብዛኞቹ አገር አቀፍ ተሳታፊዎች እውነታን የማፈላለግና የዕርቅ ሥራ ወይም ሒደት፣ የሁሉም ባለድርሻ አካላት ውክልናና ተሳትፎ ባረጋገጠ መንገድ በሚመሠረት አዲስ የእውነት አፈላላጊ ተቋም አማካይነት መካሄድ እንዳለበት ሐሳብ ሰጥተዋል፤ በየትኞቹ አጥፊዎች ላይ ክስ ሊመሠርት ይገባል በሚለው አማራጭ አብዛኞቹ ተሳታፊዎች ከፍተኛ ደረጃ ተሳትፎ ባላቸው አጥፊዎች ላይ ያተኮረ የክስ ሒደት ሊኖር እንደሚገባ መናገራቸውም ተብራርቷል።

ምሕረትን ለመተግበር የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎችን በተመለከተ አብዛኞቹ ተሳታፊዎች የምሕረት ቅድመ ሁኔታዎች በግልጽ ሊቀመጡና ከሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 28 ጋር፣ እንዲሁም ከዓለም አቀፍ ሕግ ድንጋጌዎች ጋር የተጣጣሙ ሊሆኑ እንደሚገባ እንደሚፈልጉ ተገልጿል። አብዛኞቹ ተሳታፊዎች ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ወይም ከባድ ወንጀሎችን የፈጸሙ አጥፊዎች ለምሕረት ብቁ ሊሆኑ እንደማይገባ መናገራቸውም፤ ምሕረት የመስጠት ኃላፊነት አዲስ በሚቋቋም የሀቅ አፈላላጊ ኮሚሽን አማካይነት ሊሆን እንደሚገባ ፣ ጥቂት ተሳታፊዎች ደግሞ ሒደቱ በኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽንና በአገራዊ የምክክር ኮሚሽን በኩል ቢከናወን የሚል ሐሳብ ማቅረባቸቸው፤ የማካካሻ ሒደቱ በየትኞቹ ተጎጂዎች ላይ ትኩረት ሊያደርግ ይገባል በሚል ለቀረበው አማራጭ የፖሊሲ ሐሳብ፣ በመርህ ደረጃ ለሁሉም ተጎጂዎች እንደ የጉዳቱ ዓይነትና መጠን ማካካሻ መስጠት እንደሚያስፈልግ ተሳታፊዎች ይፈልጋሉ ተብሏል።

> **የሽግግር ፍትሕ ከመደበኛው የፍትሕ ሂደት ጋር ጎን ለጎን የሚሄድ እንጂ የሚተካ አይደለም። የሽግግር ፍትሕ ተፈጻሚነቱ በተለምዶ በዝቅተኛ ደረጃ በደል በፈጸሙት ግለ ሰቦች ላይ እንጂ በዋነኞቹ (ባለ ሥልጣናት) መብት ጣሾች ላይ አይደለም። እነሱ በመደበኛው ወይም በልዩ ችሎት ይዳኛሉ**

የጅምላ ግድያ በተፈጸመባቸው ቦታዎች ሐውልት፣ ማስታወሻ ወይም ሙዚየም በማቆምና የገንዘብ ካሳን በሚያካትት አግባብ ሊከናወን እንደሚገባ ከተሳታፊዎች ሐሳብ መቅረቡ ተጠቅሷል። የማካካሻ ሥርዓቱ አዲስ በማቋቋም ኮሚሽን አማካይነት ሊመራ እንደሚገባ አብዛኞቹ ተሳታፊዎች የገለጹ መሆናቸውን፣ የሽግግር ፍትሕ የጊዜ ማዕቀፍ የት ይጀመር ለሚለው ለክስ ጉዳይ ከ1987 ጀምሮ ለእውነት ማፈላለግ፣ ዕርቅ ማስፈንና ለማካካሻ ጉዳይ፣ ነገር ግን መረጃና ማስረጃ እስከተገኘበት ጊዜ ሊዘረጋ ይገባል የሚል ሐሳብ ተነስቷል።

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽንና የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሰብዓዊ መብቶች ቢሮ በሽግግር ፍትሕ ሪፖርት ላይ ከሰሞኑ ባወጡት በጋራ ባወጡት ሪፖርት፣ በተጎጂዎች ፍላጎትና ቅድሚያ በሚሰጧቸው ጉዳዮች ላይ ጠንካራ ትኩረት በማድረግ፣ ያለፉ ጥሰቶችን የሚመጥን ምላሽ ለመስጠት፣ ፍትሐዊና ሰላማዊ የወደፊት ነገን ለመመሥረት፣ እንዲሁም አገራዊ አንድነትን ለማጎልበት፣ እውነተኛ፣ ሁሉን አቀፍና የተሟላ የሽግግር ፍትሕ ሒደት ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን የአማርኛው ሪፖርተር በዘገባው ያወሳል። ለመሆኑ የሽግግር ፍትሕ ማለት ምን ማለት ነው።

የኮሎምቢያ ዩኒቨርሲቲው ጆን ኤልስተር ፤"Transitional Justice in Historical Perspective"በሚል ርዕስ ባስነበበን ማለፊያ መጽሐፉ፤ የሽግግር ፍትሕ ትላንት የተጀመረ ሳይሆን የ"ዴሞክራሲ" ጽንሰ ሀሳብ መቀንቀን ከጀመረበት ከዛ ጥንታዊ ዘመን አንስቶ የነበር ነው ሲል ይሞግታል። በ411 ዓመተ ፍዳ/ዓመተ ዓለም/ እንዲሁ ከ404 እስከ 403 ዓዓ በአቴንስ በወቅቱ የነበረው "ዴሞክራሲያዊ" አካሄድ በአምባገነኖች ተገልብጦ እያለ ስራ ውለው የነበሩ ፈላጭ ቆራጭ አሰራሮች ፤ አምባገነኖች ከአገዛዝ እንዲወገዱ ሲደረግ ተሽረው የነበሩ ዴሞክራሲያዊ አካሄዶች ተመልሰው ስራ ላይ እንዲውሉ ተደርጓል።

በራሽያ የጥቅምት፣ በእንግሊዝና በፈረንሳይ ድህረ አብዮቶችም ተመሳሳይ ክስተቶች መኖራቸውን በማስረጃ ያወሳል። በቅርብ ደግሞ ከ2ኛው የዓለም ጦርነት ወዲህ ከጀርመን ናዚ፣ ከጣሊያን ፋሺዝምና ከጃፓን ሽንፈት በኋላ በዘመኑ አውድ የሚበየን የሽግግር ፍትሕ መተግበሩን ጆን ኤልስተር ያስታውሳል። በቀጣይ ዓመታት ደግሞ ሀገራችንን ጨምሮ በላቲን አሜሪካ፣ በደቡብ አፍሪካ፣ ዚምባብዌ ፣ ሩዋንዳ ፣ ቡልጋሪያ ፣ ሮማኒያ ፣ ሀንጋሪ ፣ ግሪክ ፣ ጣሊያን ፣ ስፔን ፣ ወዘተረፈ እንደየ ሀገራቱ ነባራዊ ሁኔታ የሽግግር ፍትሕ ተተግብሯል ይለናል ጸሐፊው ።

ናኦሚ ሮት አሪያዛና ሀቪየር ማሬዝኩሬና በጋራ ባሳተሙት ፤"Transitional Justice in the Twenty-First Century Beyond Truth"በተሰኘው መጽሐፋቸው ደግሞ የሽግግር ፍትሕ ወጥ የሆነና ቁርጥ ያለ ብያኔ ባይኖረውም ፤"ጨቋኝ፣ ፈላጭ ቆራጭና አፋኝ ከሆነ አጋዛዝ መወገድ ማግስት የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ፣ ግፎችና ሰቆቃዎች ከሁለንተናዊ ፍትሕ አንጻር የሚታዩበት አግባብ ነው።"ይሉናል። የሽግግር ፍትሕ ማለት በቀደመው ጨቋኝ ወይም አፋኝ አገዛዝ ወይም በአንድ ረዘም ላለ ጊዜ በተካሄደ የእርስ በርስ ጦርነት ወይም ግጭት ወቅት መሠረታዊ የሰው ልጆችን መብት የጣሱ ግለ ሰቦች ወይም ተቋማት፤ ከጦርነቱ በኋላ በዳይና ተበዳይ፣ የተለያዩ የማኅበረሰቡ አካላትን በሚወክሉ ግለ ሰቦች በተዋቀረው የማሕበረሰብ "ዳኞች" ፊት ቀርበው ይቅር የሚባባሉበት ሂደት ነው።

የሽግግር ፍትሕ አላማ በዳይና ተበዳይን ፊት ለፊት አገናኝቶ፤ በዳዩ በድርጊቱ መጸጸቱን በሕዝብ ፊት ይቅርታ ሲጠይቅና፣ ተበዳዩም፣ የበዳዩን ከልብ የመነጨ ጸጸት ተረድቶ ከልብ ይቅርታ እንዲያደርግ ሲሆን የረጅም ጊዜ ዓላማው ግን፤ የፖሊቲካም ሆነ ማኅበረሰባዊ ሥልጣንን ተጠቅሞ ሰብዓዊ ፍጡርን መበደል ወንጀል መሆኑ ታውቆ ቀጣዩ ትውልድ ተመሳሳይ ወንጀል እንዳይፈጽምና በዳይና ተበዳይም ከልብ ይቅር ተባብለው ለወደፊት ቂምና በቀል ለአገሪቷ ሰላምና ለማኅበረሰቡ ዕድገት ጠንቅ እንዳይሆኑ ለማድረግ ነው።

የሽግግር ፍትሕ ከመደበኛው የፍትሕ ሂደት ጋር ጎን ለጎን የሚሄድ እንጂ የሚተካ አይደለም። የሽግግር ፍትሕ ተፈጻሚነቱ በተለምዶ በዝቅተኛ ደረጃ በደል በፈጸሙት ግለ ሰቦች ላይ እንጂ በዋነኞቹ (ባለ ሥልጣናት) መብት ጣሾች ላይ አይደለም። እነሱ በመደበኛው ወይም በልዩ ችሎት ይዳኛሉ። በሌላ አነጋገር የበዳይና ተበዳይ ፊት ለፊት ተገናኝቶ በማኅበረሰቡ ፊት ይቅርታ መጠየቅና መቀበል በምንም መልኩ አንድን በዳይ በተለይም "የወንጀል ድርጊቶቹን ያቀነባበሩትንና የመሩትን" ከመደበኛው ፍርድ ቤት ፍትሐዊ ብይን ነፃ አያደርጋቸውም ።

የሽግግር ፍትሕ በተለምዶ ማኅበረሰብ ከሚያስተናግዳቸው የፍትሕ ሂደቶች ለየት ያለና በጥቂት አገራት ብቻ በተግባር የተተረጎመ ሲሆን ስኬታማነቱና ውጤታማነቱ ላይ ውስንነት አለበት። ካሉበት ውስንነቶች አንዱ ተበዳይን በተፈለገው ደረጃ መካስ አለ መቻሉ ነው። ይህ የፍትህ ሂደት በአፍሪካ ውስጥ በሰፊው በተግባር የተተረጎመው በደቡብ አፍሪካና በሩዋንዳ ሲሆን በመንግሥት ደረጃ እንደ ስኬት ቢቆጠርም በተበዳይ ግለ ሰቦችና ዘመዶች ዘንድ ግን ካሳ ባለመካተቱ ቅሬታ መተው አልቀረም ። ሰዎች በተፈጥሮ ተጨባጭ የሆነ ካሳ ፈላጊ ስለሆኑ በዳይና ተበዳይን ፊት ለፊት አገናኝቶ ይቅርታ አጠያይቆና አስተቃቅፎ ማለያየቱ ብቻ የተበዳዩን ውስጣዊ ቁስል ሊጠገግ አልቻለም።

የሽግግር ጊዜ ፍትሕ በመደበኛው የፍትህ ስርዓት ሊዳኙ የማይችሉ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ የሚተገበር የፍትህ ሂደት ነው። የፍትሕ ሚኒስቴር ሰነድ ደግሞ፤ የሽግግር ፍትሕ ሥርዓት መዘርጋት ዘላቂ ሰላም፣ እርቅ እና ፍትሕ በማስገኘት ረገድ ውጤታማ መሆኑንና በግጭት፣ በጦርነት ወይም በሌላ ምክንያት ለተፈፀሙ ጥቃቶች፣ መጠነ ሰፊ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች እና በደሎች የተሟላ መፍትሔ ይሰጣል ሲል ይተነትናል። ለሐገሪቱ የታሰበው የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ የሚመራበትንና ሥራ ላይ ሚውልበትን የማስፈፀሚያ ስልቶቹ ፣ ክስ ፣ እውነትን ማፈላለግ እና ይፋ ማድረግ ፣ ይቅርታና እርቅ ፣ ምህረት እና ካሳን ያካተተ ነው ።

የሽግግር ፍትሕ ሥርዓት መዘርጋት ዘላቂ ሰላም ፣ እርቅ እና ፍትሕ በማስገኘት ረገድ ውጤታማ መሆኑንና በግጭት፣ በጦርነት ወይም በሌላ ምክንያት ለተፈፀሙ ጥቃቶች ፣ መጠነ ሰፊ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች እና በደሎች የተሟላ መፍትሔ እንደሚያመላክት የፖሊሲ ሰነድ ያትታል ። በሌሎች ሀገራት ክስ እና ቅጣት ዋነኛ የሽግግር ፍትሕ ማስተግበሪያ ስልቶች ሆነው መታየታቸውንም ሰነዱ ያብራራልና ፖሊሲው ግን ከክስ እና ቅጣት ባለፈ እውነት እየተጣራ ይፋ የሚሆንበት፣ ዘላቂ እርቅ የሚሰፍንበት፣ የማካካሻ እርምጃ እና የተቋማት ለውጥ የሚካሄድበት ነው ።

የፖሊሲው አጥኚ ቡድን አባል አቶ ምስጋናው ሙሉጌታ ፤ የሽግግር ፍትሕ በሚከተሉት ዋና ዋና ምክንያቶች አስፈላጊ መሆኑን ያወሳሉ ። ኢትዮጵያ የምትገኝበት ሀገራዊ አውድ ማለትም የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ፣ አለመረጋጋት፣ ግጭትና የእርስ በርስ ጦርነት በመቀጠሉ ዜጎች ለሞት፣ ለመፈናቀል አደጋ እየተጋለጡ በመሆኑና ለነዚህ ችግሮች ከዚህ በፊት የተሰጡ ምላሾች ሙሉ አለመሆናቸው የአጥፊዎችና የተጎጂዎችን ቁጥር ማብዛቱ ፣ የበደሎች መደራረብ እና የጥፋቶች ማህበረሰባዊ ቅርጽ መያዝ በመደበኛው የፍትሕ ሥርዓት እና አካሄድ ፍትሕ መስጠትንም ሆነ ይቅርታ እና እርቅን ማከናወን አላስችል ማለቱ የመጀመሪያው ነው ።

የተሳካ የሽግግር ፍትሕ ለሀገረ - መንግሥት ግንባታ ወሳኝ በመሆኑ ማለትም ባለፉ በደሎች ይቅር ለመባባልና እርቅ ለማውረድ ብሎም እየተከፋፈለ ያለውን ሕዝብ ለማቀራረብ ግንኙነትን ለመጠገን ፣ ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ እና እርቅን ለማውረድ ለዚህም የሰውን ክብር ለመመለስ፣ ላለፈ ቁስል እውቅና ለመስጠት እንዲሁም ለዳግም ውህደት ማነሳሳት ሁለተኛው ዓላማ ሲሆን የተሳካ የሽግግር ፍትሕ ሂደት ሳይተገበር የዴሞክራሲ ሽግግርም ሆነ ዘላቂ ሰላም ማስፈን የማይቻል መሆኑ እንዲሁም ሰብዓዊ መብቶችን ለማስከበር እና የሕግ የበላይነትን ለማስፈን የሚያግዝ መሆኑ ሶስተኛው ሲሆን አራተኛው ዓላማ ደግሞ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለማስፈን ያለው የማይተካ ሚና ነው ።

ነገር ግን በሽግግር ፍትሕ ውስጥ የገለልተኛ ወገን ተሳትፎ መሠረታዊ ጥያቄ ነው ። ይህንን የሽግግር ጊዜ ፍትሕ ማስፈፀሚያ ሆነው ከቀረቡ ስልቶች ደግሞ ዋነኛው ክስ ነው። ማን ይከሰሳል የሚለውም ዋነኛ ነጥብ ነው። እውነትን ማፈላለግ እና ይፋ ማድረግ፣ እርቅ ፣ ምህረት፣ ማካካሻ ወይም ለደረሱ የመብት ጥሰቶች ብሎም የሀብት ውድመቶች ውጤታማና ተመጣጣኝ የገንዘብ ወይም ሌላ ካሳ ፣ መጠገኛ ፣ ማደሻ ማገገሚ አፈጻጸምን በተመለከተ የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲው ያካትታል።

ሻሎም ! አሜን ።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
ዘመን
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጻችንና ፌስቡክ ገጻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት:- www.press.et
ፌስቡክ:- Ehiopian Press Agency

# አዲስ ዘመን ማክሰኞ ስፖርት

ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# በአፍሪካ ዋንጫ ዛሬ ሶስት ጨዋታዎች ይደረጋሉ

**ብርሃን ፈይሳ**

34ኛው የአፍሪካ ዋንጫ ከተጀመረ ዛሬ አራተኛ ቀኑን አስቆጥሯል፡፡ ኮትዲቯር ለሁለተኛ ጊዜ እያስተናገደች ባለችው በዚህ ውድድር ላይ የመክፈቻው ጨዋታ ጊኒ ቢሳውን በማሸነፍ የጀመረች ሲሆን፤ በቀጣዩ ቀን ደግሞ የምድቡ ቡድን የሆኑት ናይጄሪያ እና ኢኳቶሪያል ጊኒ በአቻ ተለያይተዋል፡፡ በሌላኛው ምድብ ግብጽና ሞዛምቢክም በተመሳሳይ አቻ ሲለያዩ ኬፕቨርዴ ጋናን 2 ለ1 በሆነ ጠባብ ልዩነት ያልተጠበቀ አሸናፊነትን ተቀዳጅታለች፡፡

ትናንት በተደረገው የምድብ ጨዋታም በምድብ ሶስት ሴኔጋል ከጋምቢያ እንዲሁም ካሜሮን ከጊኒ ተጋጥመዋል፡፡ አልጄሪያ እና አንጎላ ደግሞ በአራተኛው ምድብ ጨዋታቸውን ያከናወኑ ቡድኖች ናቸው፡፡ ዛሬ በዚሁ ምድብ አንድ ጨዋታ የሚከናወን ሲሆን፤ ከምድብ አምስት ደግሞ ሁለት ጨዋታዎች ይደረጋሉ፡፡ በዚህም መሰረት የመጀመሪያው ጨዋታ በቡርኪና ፋሶ እና ሞሪታኒያ መካከል ስታዴ ዴ ላ ፔክስ በተባለውና 40ሺህ ታዳሚ በሚይዘው ስታዲየም ይካሄዳል፡፡

በ33ኛው የአፍሪካ ዋንጫ አራተኛ ደረጃን ይዞ ያጠናቀቀው የቡርኪና ፋሶ ብሄራዊ ቡድን በዚህ የአፍሪካ ዋንጫ ካለፈው ጊዜ በተሻለ ብቃት የተመለሰ ይመስላል፡፡ በአውሮፓ ክለቦች የሚጫወቱ በርካታ ተጫዋቾች ያሉትና ሶስት ጊዜ ለፍጻሜ የደረሰው ይህ ቡድን ቀላል ግምት የማይሰጠው ሲሆን፤ ለዋንጫ መድረስ ባይችል እንኳን ለትልልቆቹ ቡድኖች ሳይቀር ፈታኝ ተፎካካሪ እንደሚሆን ይገመታል፡፡ የእንግሊዝ ፕሪምየር ሊግ ክለብ በሆነው ሉተን ታውን የሚጫወተው የቡርኪናፋሶው ኢሳ ካቦሬ የቡድኑ ቁልፍ ተጫዋች ሲሆን፤ በዚህ የአፍሪካ ዋንጫ ላይ ይደምቃሉ ተብለው ከተለዩ ተጫዋቾች መካከልም አንዱ ነው፡፡ የአስቶንቪላው በርትራንድ ትራዮሬ በክለቡ ተሰላፊነት የተቀዛቀዘ ቢሆንም ለሃገሩ ግን ከዚህ ቀደም ባስቆጠራቸው 17 ግቦች ላይ ከመጨመር ወደ ኋላ አይልም፡፡ ሞሪታኒያ በበኩሏ የአፍሪካ ዋንጫ ተሳትፎ ስኬቷ ይህ ለሶስተኛ ጊዜ ነው፡፡ ሁለቱ ቡድኖች በተለያዩ ጊዜያት እርስ በእርስ ተገናኝተው አምስት ጊዜ በማሸነፍ ቡርኪና ፋሶ የበላይነቱን ትይዛለች፡፡ ይህም የጨዋታው የበላይነት የቡርኪና ፋሶ የመሆን እድሉ የሰፋ እንደሚሆን በስፖርት ቤተሰቡ ዘንድ የሚጠበቅ ነው፡፡




ቱኒዚያ ከናሚቢያ የሚያደርጉት ጨዋታ ደግሞ በአማዱ ጎን ኩሊባሊ ስታዲየም የሚከናወን ነው፡፡ 20 ሺህ ተመልካቾችን በሚይዘው በዚህ ስታዲየም በሚደረገው ጨዋታም የአሸናፊነት ቅድመ ግምቱ ወደ ሰሜን አፍሪካዊቷ ሃገር ያደላ ሆኗል፡፡ በደቡብ አፍሪካ ለምትገኘው ናሚቢያ ይህ አራተኛ የአፍሪካ ዋንጫ ተሳትፎዋ የሆነው ናሚቢያ ከምድቧ የዘለለ ታሪክ የሌላት ሲሆን፤ ይህ ተሳትፎዋ ከ11 ዓመታት በኋላ የተገኘ ነው፡፡ "ተዋጊዎቹ" የሚል ከባድ ቅጽል ስምን የተሸከመው ቡድኑ ባለፉት የአፍሪካ ዋንጫ ተሳትፎዎቹ አንድም ግብ ከመረብ ባለማሳረፍም ይታወቃል፡፡ በአንጻሩ የካርቴጅ ንስሮቹ በመድረኩ በርካታ የተሳትፎ ታሪክ ያላቸውና እአአ በ2004 ውድድሩን በማዘጋጀት ዋንጫውን ማስቀረት ችለዋል፡፡ በካሜሮኑ የአፍሪካ ዋንጫም ጠንካራ የፍጻሜ ተፋላሚ ሆነው በመቅረብ አራተኛ ደረጃን ይዘው ነበር ያጠናቀቁት፡፡ በማጥቃት ላይ የተመሰረተ ኳስ የሚጫወተው የቱኒዚያ ብሄራዊ ቡድን በዛሬው ጨዋታም ናሚቢያን አሸንፎ የመጀመሪያውን ሶስት ነጥብ እንደሚያስመዘግብ ነው የሚገመተው፡፡

በጨዋታ መርሃ ግብሩ መሰረት በተመሳሳይ ስታዲየም የሚደረገው ቀጣዩ ጨዋታ ደግሞ የማሊና ደቡብ አፍሪካ ብሄራዊ ቡድኖች ነው፡፡ በካሜሮኑ የአፍሪካ ዋንጫ ላይ ያልተሳተፉት ባፋና ባፋናዎቹ ወደ ናፈቁት መድረክ የተመለሱ ሲሆን፤ ከሌላኛው የምድቡ ጠንካራ ቡድን ጋር ይፋለማሉ፡፡ ደቡብ አፍሪካ በውድድሩ ጠንካራ ቡድን ካላቸው ሃገራት መካከል የምትመደብ እንደ መሆኗ ከምድቧ አልፋ 16ቱን የምትቀላቀል ትሆናለች በሚል ብትጠበቅም በአውሮፓ ክለቦች በሚጫወቱ ተጫዋቾች የተዋቀረው የማሊ ቡድን ግን በቀላሉ እጅ የሚሰጥ አይሆንም፡፡ አንድ ጊዜ ዋንጫውን ያነሱት ባፋና ባፋናዎች ሁለተኛ እና ሶስተኛ ደረጃን ይዘው ያጠናቀቁበት ሌላኛው የስኬት ታሪካቸው ሲሆን፤ ያለፈው ተሳትፏቸው ግን የተጠናቀቀው በሩብ ፍጻሜ ነበር፡፡

በምድቧ የመጀመሪያ ጨዋታ ተሸንፋ የማታውቀው ማሊ በበኩሏ በረጅም ጊዜ የተሳትፎ ታሪኳ ዋንጫውን ባታነሳም "የተሻለ" የሚባል ተሳትፎ አላት፡፡ እአአ በ2021ዱ የካሜሮን አፍሪካ ዋንጫ ግን ከ16ቱ ማለፍ በመቻሏ በጊዜ ነበር ከውድድሩ የተሰናበተችው፡፡ ይሁንና፣ በዛሬው ጨዋታ ላይ ነጥብ በማስመዝገብ ጠንካራ ቡድን መሆኗን ዳግም የምታስመሰክርበትን አጨዋወት ይዛ እንደምትታይ ይጠበቃል፡፡

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን
Ethiopian Cooperative Commission
(ECC)

## ከኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ጋር በመተባበር
### በየሳምንቱ የሚታተም

# ኅብረት ሥራ ማህበራት በአዲስ ምዕራፍ

**ኢያሱ መሰለ**



ኅብረት ሥራ ማህበራት በመንግሥትና በግሉ ዘርፍ ሊሸፈኑ የማይችሉ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ክፍተቶችን የመሙላት ተልዕኮ ይዘው ወደ ሥራ ከገቡ ጊዜ ጀምሮ በርካታ አስተዋጽኦዎችን አበርክተዋል:: ይሁንና የሀገራችን ኅብረት ሥራ ማህበራት በሚኖራቸው አዎንታዊ አስተዋጽኦ ፈጣሪነት ከሌሎች ሀገራት ጋር ሲነጻጸሩ ገና ብዙ መሥራት እንዳለብን ይታመናል:: በተለይም አሁን ካለው የሀገራችን እና የዓለም ነባራዊ ሁኔታ አንጻር የሀገራችንን ኅብረት ሥራ ማህበራት አቅም ማጠናከር ከምን ጊዜውም በላይ አስፈላጊ ሆኗል:: በመሆኑም የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ማህበር የማህበራቱን አደረጃጀትና አሠራር በማዘመን የተወዳዳሪነት አቅም እንዲኖራቸው ለማስቻል የማሻሻያ( የሪፎርም) ሰነዶችን አዘጋጅቶ በየደረጃው ላሉ ባለድርሻ አካላት ሲያስተዋውቅ ሰንብቷል:: በመጨረሻም በታላቅ ሀገራዊ መድረክ ላይ ሪፎርሙን አብስሯል::

በዚሁ መሰረት ‹‹የሀገር አቀፍ የኅብረት ሥራ ማህበራት ልማትና እድገት የሪፎርም ንቅናቄ ማብሰሪያ መርሃ-ግብር ታህሳህ 28 2016 ዓ.ም በስካይ ላይት ሆቴል በታላቅ ድምቀት ተከናውኗል:: ‹‹ከገበያ በላይ!›› ( BEYOND THE MARKET!) በሚል መሪ ሃሳብ በተከናወነው በዚህ የማብሰሪያ መርሃ-ግብር፣ የምክር ቤት አባላት ፣ የጠቅላይ ሚንስትር ጽህፈት ቤት ተወካዮች ፣ የብልጽግና ጽህፈት ቤት ኃላፊዎች ፣ሚኒስትሮች፣ የክልል ፕሬዚዳንቶች፣ የኅብረት ሥራ ማህበራት ኃላፊዎችና ተወካዮች ፣ የባንክ አመራሮች፣ የዩኒቨርሲቲ ተወካዮችና ሌሎችም ተገኝተዋል::

በመርሃ -ግብሩ የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ማህበር ዋና ኮሚሽን ኮሚሽነር ጌታቸው መለሰ (ዶክተር) የእለቱን ዋና ጉዳይ ካስተዋወቁ በኋላ የኅብረት ሥራ ማህበራትን ታሪካዊ አመጣጥ ጠቅሰው የሀገራችን የኅብረት ሥራ ማህበራትም እንደሌሎች ሀገራት ኅብረት ሥራ ማኅበራት አቅም ሊኖራቸው ያስፈልጋል ብለዋል:: በመሆኑም ኅብረት ሥራ ማህበራት ለሀገር በቀል ኢኮኖሚ ግንባታ አጋዥ እንደመሆናቸው ያሉባቸው ማነቆዎች ተወግደው ውጤታማ ሥራ እንዲሠሩ ሪፎርም ማድረግ እንዳስፈለገ ገልጸዋል::

ሪፎርሙ በአጭርና በረዥም ጊዜ እንደሚተገበር የተናገሩት ዋና ኮሚሽነሩ በዚህ ዓመት እንዲተገበሩ የተለዩትም የኅብረት ሥራ ማህበራት በግብርና ግብዓትና አገልግሎት፣ በምርት ገበያ፣ በእሴት ጭመራ እንዲሁም ምርትን በስፋት በማቅረብና በማስተዋወቅ ፣በመሰረተ ልማት አቅርቦት፣ የአክሲዮን ካፒታል በማሰባሰብና የኅብረት ሥራ ባንክ በማቋቋም ላይ ያነጣጠሩ ሥራዎች እንደሚሠሩ ጠቁመዋል::

የኅብረት ሥራ ማህበራት ጠንካራ አደረጃጀትና ወጥ አደረጃጀት እንዲኖራቸው፣ የአመራር ሥርዓታቸው እንዲሻሻል፣ የኦዲት፣ የኢንስፔክሽን፣ የብቃትና እውቅና ደረጃ አሰጣጥ በተሟላ የፖሊሲ ማዕቀፍና የአሠራር ሥርዓት እንዲተገበር ይሠራል ብለዋል::

የእውቀት፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር፣ የሰው ኃይል ልማትና የልምድ ልውውጦችን እንዲያገኙ በማድረግ ሀገር አቀፍ የኅብረት ሥራ ማህበራት ሊግን ለመፍጠር መታሰቡንም አስረድተዋል::

እነዚህ ቁልፍ የሪፎርም ተግባራት ተፈጻሚ ሲሆኑ ዘመናዊ አደረጃጀት ያላቸው፤ በሰለጠነ የሰው ኃይል የሚመሩና በቴክኖሎጂ የታገዘ አገልግሎት የሚሰጡ፤ በምርቶች ላይ ተገቢውን የገበያ ዋጋ የመወሰን ብቃት ያላቸው ፤ ለከተማና ገጠር ትስስር መጠናከር ፤ ለኢንዱስትሪዎች መስፋፋትና እድገት የድርሻቸውን ሚና የሚወጡ፤ ገበያን የማረጋጋት ሚና ያላቸው፤ በሀገር ውስጥ እና ዓለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪ የሆኑ ኅብረት ሥራ ማህበራት ይፈጠራሉ ሲሉ ተናግረዋል::

በመጨረሻም ከፌደራል እስከ ወረዳ ያሉ የሴክተሩ አጋሮች፤ መንግሥታዊና ዓለም አቀፍ ተቋማት ለሀገሪቱ እድገት ወሳኝ ለሆነው የሪፎርም ንቅናቄ ውጤታማነት ክትትላቸውና ድጋፋቸው አስፈላጊ መሆኑን በመጥቀስ ለሪፎርሙ ተተግባሪነት አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ዋና ኮሚሽነሩ ዶክተር ጌታቸው መለሰ ጥሪ አቅርበዋል::

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር አቶ ሺሰማ ገብረስላሴ የኅብረት ሥራ ማህበራትን ታሪካዊ አመጣጥ ፤ የሀገራትን ተሞክሮዎችና፣ የሀገራችን የኅብረት ሥራ ማህበራት አሁን ያሉበትን ደረጃ፤ እንዲሁም የሪፎርሙን አስፈላጊነት በተመለከተ በተዘጋጀው የመወያያ ሰነድ ላይ ማብረራሪያና ገለጻ ሰጥተዋል:: የቀረበውን የሪፎርም ሰነድ መነሻ በማድረግም ተሳታፊዎች በሰፊው የመከሩ ሲሆን ለሪፎርሙ ተጨማሪ አቅም የሚፈጥሩ የማጠናከሪያ ሀሳቦች ከታዳሚዎቹ ተገኝተዋል::

የውይይት መድረኩን የመሩት የግብርና ሚኒስቴር ሚኒስትር እና የሪፎርም ኮሚቴው ሰብሳቢ ዶክተር ግርማ አመንቴ ባስተላለፉት መልዕክት ኅብረት ሥራ ማህበራት የዜጎችን የተናጠል ጉልበት ፣ ገንዘብና እውቀት በማሰባሰብ በግሉና በመንግሥት የኢኮኖሚ ዘርፍ መካከል የሚፈጠረውን ጉድለት ለመሙላትና የገበያ ሚዛን ለመጠበቅ የተቋቋሙ ፤ እንደ ሶስተኛ የኢኮኖሚ ዘርፍ ተደርገው የሚወሰዱ መሆኑን ጠቅሰዋል::

ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ተጠሪነቱ ለግብርና ሚኒስቴር እንደመሆኑ ኅብረት ሥራ ማህበራት በተለይም የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ለውጪ ምንዛሪ እና ለኢንዱስትሪ ጥሬ እቃ ዋነኛ ምንጭ በመሆን የሚያገለግለውን የግብርና ክፍለ ኢኮኖሚ ለማሳደግ የማይተካ ሚና ያላቸው መሆኑን ተናግረዋል:: ሆኖም ግን በሀገራችን ያሉ ኅብረት ሥራ ማህበራት በብዙ ተግዳሮቶች የተከበቡ በመሆናቸው ዘርፉ በሚፈለገው ደረጃ ማደግ አልቻለም ብለዋል:: የሀገራችን የኅብረት ሥራ ማህበራት ከሌሎች መሰል ሀገራት አንጻር ሲታዩ የገበያ ድርሻቸውና ተጽዕኖ ፈጣሪነታቸው ዝቅተኛ እንደሆነ ጠቅሰው፤ ይህን ቀልብሶ ውጤታማነታቸውን ማረጋገጥ ጊዜ የማይሠጠው ጉዳይ እንደሆነም አስምረውበታል::

በመሆኑም ኅብረት ሥራ ማህበራት የካፒታል አቅማቸውን አጠናክረው የአርሶ እና አርብቶ አደሩን የግብርና ግብዓት አቅርቦት በማሻሻል ምርት እና ምርታማነትን ማሳደግና የሀገር ውስጥ እና የውጭ ገበያ ድርሻቸውን ማሻሻል እንዲችሉ ሪፎርሙ ለውጥ ያመጣል የሚል እምነት በመያዝ የሌሎች ሴክተር አመራሮችም ለኅብረት ሥራ ሴክተር ሪፎርም ስኬታማነት ድጋፍ እንዲያደርጉ ሚኒስትሩ ጥሪ አቅርበዋል::

አድራሻ | የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን | 0115573448/ 0118592105 | ፖ.ሳ.ቁ. 19787 | Facebook: Ethiopia cooperative Commission | Website: www.fca.gov.et

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ